# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 279 ሰኔ 9 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# የሱዳን የሰላም ድርድር በአዲስ አበባ እንዲካሄድ ውሳኔ ተላለፈ

**ሞገስ ጸጋዬ**



ፎቶ፡ አሸናፊ ጉደታ

አዲስ አበባ፡- ሰኔ አምስት በጂቡቲ የተካሄደው የኢጋድ 14ኛው መደበኛ የመሪዎች ስብሰባ የሱዳን የሰላም ድርድር በአዲስ አበባ እንዲካሄድ ውሳኔ ማስተላለፉን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በትናንትናው ዕለት መደበኛ ሳምንታዊ ጋዜጣዊ መግለጫውን ለአገር ውስጥና ለውጭ አገራት መገናኛ ብዙኃን ሰጥቷል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም ሳምንታዊ ዲፕሎማሲያዊ ክንውኖችን አስመልክቶ እንደገለጹት፤ ያለፈው ሳምንት ሰፊ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ የተደረገበትና ኢትዮጵያ ከበርካታ አገራት ተወካዮች ጋር የሁለትዮሽ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያካሄደችበት በመሆኑ ስኬታማ ነበር ብለዋል።

ኢጋድ ከሱዳን አንጻር ከፍተኛ ሥራ ሠርቷል ያሉት አምባሳደሩ፤ በመሪዎች ደረጃ በዝርዝር ለመነጋገር ዕድል የሰጠ ስብሰባ ነበር። ኢትዮጵያን ጨምሮ አራት አገራት ለሱዳን መፍትሔ እንዲያፈላልጉ ውክልና ሰጥቷል። በአስር ቀናት ውስጥ የሁለቱንም ተወካዮች ለማግኘት እቅድ አለ፤ የቀጣይ የሰላም ሂደት ድርድሩ በአዲስ አበባ እንዲካሄድም ውሳኔ ተላልፏል፤ ይህ ታሪካዊ ውሳኔ ተደርጎ ይወሰዳል።ኢትዮጵያ ለሱዳን ሰላም የረጅም

የሱዳን የሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## «ኢፕድ ለተቋማት የሚሰጠው ሥልጠና ዋና ዓላማው ማኅበረሰባዊ ለውጥ ማምጣት ነው»

*- ዶክተር አሸናፊ አበራ*

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ኢፕድ በሥልጠና ማዕከሉ ለተቋማት የሚሰጠው ሥልጠና ዋና ዓላማው ማኅበረሰባዊ ለውጥ ማምጣት ነው ሲሉ ዶክተር አሸናፊ አበራ ገለጹ።

ኢፕድ በሥልጠና ማዕከሉ "ትጋት፣ ዕውቀት፣ ፈጠራና ትብብር ለውጤት" በሚል መሪ ሀሳብ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አመራሮችና ሠራተኞች ሲሰጥ የነበረው ሥልጠና በትናንትናው ዕለት ተጠናቋል። በመርሐግብሩ "የሥራ ላይ ሥነ-ልቦና እና ምላሽ አሰጣጥ" በሚል ርዕሰ ጉዳይ ሥልጠና የሰጡት መምህርና

«ኢፕድ ለተቋማት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## «ሕዝቡ ለአብሮነቱና ለአንድነቱ ጽኑ ፍላጎት ያለው ለመሆኑ ሀገራዊ ምክክሩ ትልቅ ማረጋገጫ ነው»

*- ረዳት ፕሮፌሰር ምሕረቱ ሻንቆ*
*የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ*

**ዋቅሹም ፍቃዱ**



አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመመካከር መወሰኑ በራሱ አብሮነቱንና አንድነቱን ከማስቀጠል የመነጨ ጽኑ ፍላጎት ያለው መሆኑን ማሳያ ነው ሲሉ የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ ረዳት ፕሮፌሰር ምሕረቱ ሻንቆ ገለጹ።

ሚኒስትር ዴኤታው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ ለመመካከር ፍላጎት ያለው ቡድን፣ ግለሰብ ወይም ሕዝብ ካለ ቀሪውን ረጅም መንገድ አብረው መጓዝ ይችላሉ።ለአጭር ጊዜ የጋራ ጉዞ ወይንም ለጋራ ቆይታ ሰፊ ምክክር እምብዛም አያስፈልግም።እንደ ሟርተኞች ሟርት ኢትዮጵያ የምትፈርስ አገር ሳትሆን አንድነቷን አስጠብቃ ትዘለቃለች።ለዚህም ነው ሕዝቦቿ በሙሉ ልባቸው ለምክክር እየተዘጋጁ ያሉት።

«ሕዝቡ ለአብሮነቱና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ደረሰኝ አልባ ንግዶችና ግብር

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በገበያ ቦታዎች፣ በሱቆች፣ በሬስቶራንቶች እና በሌሎችም የመገበያያ ሥፍራዎች ገዥና ሻጭ በዋጋ ተደራድረው እና ተስማምተው ይገበያያሉ:: በተለይ አዲስ አበባ የዚህ ትዕይንት ጎልቶ የሚታይባት ከተማ ነች::

ሆኖም በግብይት ሥርዓት ውስጥ ደረሰኝ መስጠትና መቀበል ሊዘነጉ እና ችላ ሊባሉ የማይገባቸው ወሳኝ ነገሮች ቢሆንም በመዲናዋ ግን የተለመዱ ተግባራት ሆነዋል:: ግብርን በመሰወር ለግል ጥቅሙ ብቻ የሚሯሯጥ ሻጭ፤ ደረሰኝ ባይቀበል ምንም የማይመስለው ገዢ መበራከቱ እየታየ ነው::

ኮተቤ አካባቢ ከአንድ ሱፐር ማርኬት በርከት ያለ የቤት አስቤዛ ገዝተው ሲወጡ ያገኘናቸው ወይዘሮ ሃና በርሄ (ስማቸው የተቀየረ) በግብይት ወቅት ደረሰኝ መስጠትም ሆነ መቀበል ግዴታ መሆኑን አውቃለሁ ይላሉ::

ሆኖም "ደረሰኝ ብጠይቅ ባልጠይቅ እኔ ብቻ ብጨቃጨቅ ምን ለውጥ ይመጣል" ባይ ናቸው:: በርካታ ንግድ ቤቶች ያለደረሰኝ እንደሚሸጡ የሚናገሩት ወይዘሮ ሃና፤ ደረሰኝ በሚጠየቁበት ጊዜ በጥርጣሬ እንደሚመለከቷቸውም ይናገራሉ::

አብዛኞቹም ማሽን ተበላሸ የሚል እና ሌላ ተመሳሳይ ምላሽ ስለሚሰጡ ባልጠይቅ ይሻላል ብለው ወስነው መተዋቸውን ነው የሚናገሩት::

ሌላኛው አራት ኪሎ አካባቢ በሚገኝ አንድ

ደረሰኝ አልባ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል
















# በቀን ለ30 ሕፃናት የዓይን ሕክምና አገልግሎት የሚሰጥ ማዕከል ሊገነባ ነው

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- በቀን ለ30 ሕፃናት የዓይን ሕክምና አገልግሎት የሚሰጥ ማዕከል ሊገነባ መሆኑን የአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አስታወቀ።

በአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በቀን ለ30 ሕጻናት አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የሕጻናት ዓይን ሕክምና ማዕከል ለመገንባት በትናንትናው ዕለት የመሠረት ድንጋይ ተቀምጧል።

በመርሐ ግብሩ ላይ በአለርት ሆስፒታል የዓይን ሕክምና ክፍል ኃላፊ ዶክተር ሰለሞን ቡሳ እንደገለፁት፤ በሀገሪቱ የሚገኙት የሕጻናት ዓይን ሕክምና ስፔሻላይስድ ሆስፒታል ሦስት ብቻ በመሆናቸው ከፍተኛ የሆነ የሕጻናት ዓይን ሕክምና ተቋማት እጥረት አለ።

በመሆኑም የሕጻናት ዓይን ሕክምና ማዕከል ተደራሽነትን ማስፋት እና በቀን ለ30 ሕጻናት አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የሕጻናት ዓይን ሕክምና ማዕከል ሊገነባ መሆኑ ችግሩን ለመቅረፍ አዎንታዊ አስተዋፅዖ አለው ብለዋል።

የግንባታው ወጪ 60 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር ሰለሞን፤ ክርስቲያን ብላይንድ ሚሽን (ሲቢኤም) የተባለው የጀርመን ተራድዖ ድርጅት ሙሉ በሙሉ ወጪውን እንደሚሸፍን አስታውቀዋል።

የማዕከሉን ግንባታ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ለማጠናቀቅ እቅድ የተያዘ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀን ለ30 ሕጻናት የሕክምና አገልግሎት መስጫ፣ የተኝቶ ሕክምና፣ የቀዶ ጥገና፣ የማስተማሪያ፣ የሕጻናት ማቆያና ሌሎችም ክፍሎች እንደሚኖሩት አስረድተዋል።

በተጨማሪም በተንቀሳቃሽ ስማርት ስልክ መተግበሪያ በአንድ ትምህርት ቤት በአንድ ጊዜ ከአንድ ሺህ በላይ ተማሪዎችን የመነጽር ምርመራ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ይገኛል ያሉት ኃላፊው፤ መነጽር ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በነፃ እየተሰጠ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

በሀገሪቱ የሕጻናት ዓይን በሽታ እየተስፋፋ ነው ያሉት ዶክተር ሰለሞን፤ ችግሩን ለመፍታት የሕጻናት ዓይን ሕክምና ተቋማትን መገንባትና ባለሙያዎችን ማሰልጠን አስፈላጊ መሆኑን አስገንዝበዋል።

በጤና ሚኒስቴር የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ሕይወት ሰለሞን በበኩላቸው፤ በሀገሪቱ የዓይን ሕክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በሦስት ደረጃዎች ያሉ ቢሆንም ካለው የሕዝብ ቁጥር አንጻር በቂ አይደሉም ብለዋል።

የዓይን ሕክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ለማስፋፋት በትኩረት እየተሠራ ነው ያሉት ዶክተር ሕይወት፤ የመጀመሪያ፣ የሁለተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ የዓይን ሕክምና ተቋማትን፣ ጤና ጣቢያዎችና ጤና ኤክስቴንሽኖች ለማኅበረሰቡ የሚሰጡትን አገልግሎት ለማስፋት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የዓይን ችግር ያለባቸው ታዳጊዎች ወደጤና ተቋማት ሄደው የሕክምና አገልግሎትና የመነጽር ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል ብለዋል።የዓይን ሕክምና ማዕከላትን ለማስፋት፣ የጤና ባለሙያዎችን ለማሣልጠን እና ለማኅበረሰቡ ግንዛቤ ለመፍጠር ሁሉም ባለድርሻ አካላት እገዛ ሊያደርግ እንደሚገባም አሳስበዋል።



አቶ ተስፋዬ ይገዙ የኦሮሚያ የንግድ ቢሮ ምክትል ኃላፊ

# የክልሉ ንግድ ቢሮ የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት እየሠራ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት እየሠራ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ንግድ ቢሮ ገለጸ።

የኦሮሚያ ክልል ንግድ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ይገዙ በትናንትናው እለት በሰጡት መግለጫ፤ የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት የእሁድ ገበያዎችን የማስፋፋት እና የንግድ ሥርዓቱን የማዘመን ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል።

የገበያ ንረቱን ለማረጋጋት የእሁድ ገበያ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ በመሆኑም በመጪዎቹ አምስት ወራት 155 ገበያዎችን ለመጨመር እቅድ ተይዞ እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል።

በኦሮሚያ ክልል 600 ወረዳዎች እንዳሉ የተናገሩት ምክትል ኃላፊው፤ እነዚህ የሚጨመሩት ገበያዎች እስካሁን ድረስ የእሁድ ገበያ ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች እና ገበያው ቢዳረስም ቁጥራቸው ዝቅተኛ በሆነባቸው አከባቢዎች እንደሆነ ተናግረዋል።

አቶ ተስፋዬ እንደገለጹት፤ በክልል በሁለት ዙር ስድስት ቡድን ያለው ግብረኃይል ተዋቅሮ በእሁድ ገበያ ላይ ጥናት የሠራ ሲሆን፤ የጥናት ግብረ ኃይሉ ሊያረጋግጥ እንደቻለው በእሁድ ገበያ የሚቀርቡት ምርቶች ከሌሎች ከአምስት እስከ 10 ብር ቅናሽ እንዳለው እና በኩንታል እስከ 600 ብር ልዩነት እንዳለው ማወቅ ተችሏል።

የእሁድ ገበያን ማስፋፋት ሸማቾች የሚገዙትን ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት እንዲችሉ ብሎም የግብይት ሰንሰለቱን በመቀነስ የአምራቹን ድካምና ወጪ ይቀንሳል ሲሉ ገልጸዋል።የዋጋ ንረቱን ለመከላከል የንግድ ሥርዓቱን ፈር የማስያዝ ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ በክልሉ 803 ሺህ የንግድ ተቋማት ላይ የቁጥጥር ሥራ ተሠርቶ 127 ሺህ የሚሆኑት የተለያዩ ችግር እንዳለባቸው ሊደረስባቸው ተችሏል ብለዋል።

በእነዚህ 127 ሺህ ንግድ ተቋማት ውስጥ ያለንግድ ፈቃድ ሲነግዱ፣ ንግድ ፈቃድ ያለጠፉ፣ ያለአግባብ ዋጋ የጨመሩ እና ዋጋ ያለጠፉ ተቋማት እንደነበሩ ጠቅሰዋል።እነዚህንም የንግድ ተቋማት ወደመስመር ለማስገባት በተሠራው ሥራ ከ100 ሺህ በላይ የሚሆኑት ወደመስመር የገቡ ሲሆን 27 ሺህ የሚሆኑት ክትትል ላይ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

የንግድ ሥርዓቱን ባላከበሩ ነጋዴዎች ላይ አስተዳደራዊ ርምጃ መወሰዱን ጠቅሰው ከቅጣቱ መንግሥት ከ61 ሚሊዮን በላይ ብር ገቢ አግኝቷል ሲሉ በመግለጫቸው አንስተዋል።

# ኢትዮጵያ ለስደተኞች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የገባችውን ቃል በአግባቡ እየፈጸመች ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ስደተኞች መድረክ ላይ የገባችውን ቃል ኪዳን በአግባቡ እየፈጸመች መሆኑን የኢፌዴሪ ስደተኞችና ከስደት ተመላሾች አገልግሎት ገለጸ።

የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ተስፋሁን ጎበዛይ እንደገለጹት፤ በፈረንጆቹ የዘመን ቀመር በ2019 በጄኔቫ የተካሄደው ኮንፈረንስ ላይ አገራት የተለያዩ ቃልኪዳኖችን ገብተው ነበር። ኢትዮጵያም በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በትምህርት ተደራሽነት፣ በማኅበራዊ ጥበቃ እንዲሁም በኃይል አቅርቦት ላይ የገባችውን ቃልኪዳን ለመፈጸም በርካታ ተግባራትን አከናውናለች።

90ሺ ለሚሆኑ ስደተኞችና ተቀባይ ማኅበረሰቦች የሥራ እድል ለመፍጠር ቃል ገብታ 129ሺ ለሚደርሱ ተቀባይ ማኅበረሰብና ስደተኞች የሥራ እድል መፍጠሯን ገልጸው፤ በትምህርት ዘርፍ 20ሺ ለሚሆኑ ስደተኞችና ስደተኛ ተቀባይ ማኅበረሰቦች የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ለመስጠት ቃል ገብታ ለ12 ሺ ሰዎች ሥልጠና መስጠት ተችሏል።

ከዚህም በተጨማሪ በጥበቃና ሕግ ማዕቀፍ ዘርፍም መንግሥት እነዚህን ተግባራት ለማከናወን የሚያስፈልጉ የሕግ ማዕቀፎችን ለማዘጋጀትና ለሌሎች ደጋፊ አካላት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በገባችው ቃልኪዳን መሠረት አስፈላጊ አዋጆችን የሕግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት አመርቂ ውጤት አስመዝግባለች ብለዋል።

ከኃይል አቅርቦት አንጻር የተከናወኑ ተግባራት ቢኖሩም አሁንም የሚቀሩ የቤት ሥራዎች መኖራቸውን አስታውሰው፤ በቀጣይ አምስት ወራት ቀሪ ሥራዎችን ለማከናወን በትኩረት እንደሚሠራ ተናግረዋል።

ተግባራትን ለመከወን ኮቪድ 19፣ በአገሪቱ የነበሩ አለመረጋጋቶችና ሌሎችም ፈተናዎች ሆነው እንደነበር አመላክተው፤ በእነዚህ ችግሮችም ውስጥም ሆና ኢትዮጵያ የገባችውን ቃልኪዳን ለመፈጸምና ለስደተኞች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እየሠራች መሆኗ አቶ ተስፋሁን ገልጸዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ኮሚሽን የኢትዮጵያ ተወካይ ዶክተር ማማዱ ዲያን ባልዴ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ስደተኞችን ተቀብላ በማስተናገድና ከለላ በመስጠት በኩል ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከተች መሆኑን ገልጸዋል።



አቶ ተስፋሁን ጎበዛይ

ባለፉት ጊዜያት በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ጫናዎች ውስጥ ነበረች ያሉት ተወካዩ፤ በእነዚህ አስቸጋሪ ጊዜያት ውስጥም እንኳን ለስደተኞች የምታደርገውን መልካም ተግባር አላቋረጠችም ለዚህም ምስጋና እናቀርባለን ብለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ አስፈላጊ የሕግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀትና በሌሎችም ተግባራት ስደተኞችን ያካተተ ሥራ ለመሥራት የሄደችበት ርቀት የሚደነቅ መሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣናው ያሉ አለመረጋጋቶች፣ ኮቪድ 19ና ሌሎችም ተፈጥሯዊ ችግሮች ባለፉት ዓመታት በርካታ ስደተኞችን እንድትቀበል አስገድዷል።እነዚህን ስደተኞች ተቀብላ ለማስተናገድ በምታደርገው ሂደት ድጋፍ ያደረጉ አጋር አካላትንም አመስግነዋል።

አሁንም በርካታ ስደተኞች በአገሪቱ በመኖራቸው አጋር አካላት የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ስደተኞችን አስጠልላ እንደምትገኝ የተገለጸ ሲሆን ስደተኞቹም በዋናነት ከደቡብ ሱዳን፣ ሶማሊያ፣ ኤርትራ እና ሱዳን የመጡ መሆናቸው ተመላክቷል።

ዜና

# ጉባኤው እንደአገር ለመድረስ የታሰበው የፋይናንስ ሥርዓት አቅጣጫን የሚያመላክት ነው

**ማሕሌት ብዙነህ**




አዲስ አበባ፡- ስድስተኛው የምሥራቅ አፍሪካ የፋይናንስ ጉባኤ እንደአገር ለመድረስ የታሰበው የፋይናንስ ሥርዓት አቅጣጫን የሚያመላክት የውይይት መድረክ መሆኑ ተገለጸ።

ለሁለት ቀናት የሚቆየው ስድስተኛው የምሥራቅ አፍሪካ ፋይናንስ ዓመታዊ ጉባኤ በትናንትናው እለት በአዲስ አበባ መካሄድ ጀምሯል።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ገመቹ ዋቅቶላ በጉባኤው ላይ እንደገለጹት፤ ጉባኤው በዋነኝነት ፋይናንስ ሴክተር ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነው። መድረኩ የፋይናንስ ሥርዓቱ ያሉበትን ክፍተቶች፣ አዳዲስ ለውጦችን እና መልካም ዕድሎች ለማየት የሚረዳ ነው። እንደሀገር ሊተገበር የሚፈለገውን የፋይናንስ ሥርዓትም የሚያመላክትም ጭምር ነው።

መድረኩ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው ያሉት ዶክተር ገመቹ፤ አካታችና ተደራሽ የሆነ የፋይናንስ ሥርዓት እንዴት ይገነባል የሚለውንና አሁን ላይ የደረሰበትን ደረጃ ለማየት ያስችላል ብለዋል።

የብሔራዊ ባንክ የፋይናንስ ተቋማት ሱፐርቪዥን ምክትል ኃላፊ አቶ ሰለሞን ደስታ በበኩላቸው፤ በአገሪቱ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ፍላጎት ያለ በመሆኑ አቅርቦት እና ፍላጎት የተመጣጠነ አይደለም። ለዚህም ያለውን አለመመጣጠን ለመፍታት መድረኩ በሀገሪቱ ያለውን የፋይናንስ ሥርዓት በጥልቀት በማየትና የተሻለ አሠራርን ለመተግበር የውይይትና የልምድ ልውውጥ የሚካሄድበት መድረክ ነው።

ባለፉት የተካሄዱት ጉባኤዎች የታዩ የጥናትና ምርምር ሀሳቦች ለሀገር መጥቀማቸውን በማስታወስ ዘንድሮም የሚካሄደው መድረክም ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት የሚያግዙ ውሳኔዎችን ለመወሰን የሚያግዝ እንደሆነ አቶ ሰለሞን ተናግረዋል።

የፋይናንስ አካታችነት፣ የቀጣናው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና የካፒታል ገበያ፣ የዲጂታል ፋይናንስ፣ በፋይናንስ ገበያ ሊበራይዜሽን በጉባኤው ላይ በዝርዝር የተዳሰሱ ጉዳዮች ናቸው።

በመድረኩ ላይ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የብሔራዊ ባንክ ተቆጣጣሪ ክፍል፣ ከኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣ ከብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ፕሮግራም እንዲሁም ከአስራ አንድ ሀገራት የተወጣጡ ከ300 በላይ በፋይናንስ ሴክተር ውስጥ ያሉ የዘርፉ ባለሙያዎችና ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ተሳትፈውበታል።

ባለፉት አምስት ዓመታት በተከታታይ በየዓመቱ የተካሄዱ ጉባኤዎች ሁለት ሺህ ተሳታፊዎች እና 500 ኩባንያዎች የተገኙበት እና ከመቶ በላይ የዘርፉ ምሑራን የጥናት ጽሑፎች ያቀረቡበትና አዳዲስ ሀሳቦች የተነሱበት መሆኑ ይታወሳል።



# በኢትዮጵያ ንጹሕ የመጠጥ ውሃና የኃይል አቅርቦት ተደራሽነትን ለማሳደግ እየተሠራ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ንጹሕ የመጠጥ ውሃና የኃይል አቅርቦትን ሙሉ ለሙሉ ተደራሽነት ለማሳደግ እየተሠራ እንደሚገኝ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የውሃና መሬት ልማት ጥበቃ ማዕከል በውሃ፣ አፈርና መሬት ሀብት ጥበቃ ዙሪያ አገር አቀፍ የጥናትና ምርምር ጉባኤ በትላንትናው ዕለት ተካሂዷል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር አስፋው ዲንጋሞ እንደገለጹት፤ መንግሥት የአሥር ዓመት የልማት ዕቅድን በማዘጋጀት ድህነትን የማጥፋትና ኢኮኖሚውን ለማፋጠን የውሃና የመሬት ሀብትን በመጠቀም ላይ ይገኛል። በዚህም ንጹሕ የመጠጥ ውሃና የኃይል አቅርቦት ተደራሽነትን ለማሳደግ እየተሠራ ነው።

እንደ አምባሳደር አስፋው ገለጻ፤ እንደ አገር በ2030 የውሃ ሀብት አስተዳደርን በማረጋገጥ ለዜጎች ንጹሕ የመጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽንና የኃይል አቅርቦትን ሙሉ በሙሉ ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ ነው።

በኢትዮጵያ ድህነትን ለመቀነስና የምጣኔ ሀብት ሽግግርን ለማምጣት የአስር ዓመት መሪ የልማት እቅድ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ለመሪ ዕቅዱ ስኬታማነት የመሬትና ውሃ ሀብትን መጠበቅ ወሳኝ ነው ብለዋል።

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመሬትን የውሃ ዘርፉን በምርምር መደገፍ ያላቸውን ሚና አጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በዩኒቨርሲቲዎችና ከተፋሰስ አስተዳደር ጽሕፈት ቤቶች ጋር በቅርበት በመሥራት ላይ መሆኑን ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ምትኬ ሞላ በበኩላቸው፤ የዩኒቨርሲቲው የውሃና የመሬት ሀብት ማዕከል በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለረጅም ዓመታት ሲሠሩ ከቆዩ አስራ አንድ የምርምር ተቋማት አንዱ መሆኑን ጠቅሰዋል።

እንደ ፕሮፌሰር ምትኬ ገለጻ፤ ዩኒቨርሲቲው ከመማር ማስተማሩ በተጨማሪ የምርምር ተቋማትን በማደራጀት ምቹ ሁኔታን በመፍጠርና ችግር ፈቺ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል። በዚህም ለአገራዊ ልማት ግንባታ የሚውሉ ጥናትና ምርምሮችን በማድረግ አስተዋፅዖውን አጠናክሮ ይቀጥላል።

ማዕከሉ የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል ያሉት ፕሮፌሰር ምትኬ፤ በጣና ዙሪያ የመሬት መራቆትን፣ የእርሻ ሥራንና በዓባይ ወንዝ ላይ የደለል መጠንን ለመቆጣጠር በተሠሩ ሥራዎች ውጤት በማስገኘት ላይ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በጥናትና ምርምር ጉባኤው ላይ ፖሊሲ አውጪዎች፣ ዲፕሎማቶች፣ የተለያዩ አገራት አምባሳደሮች፣ የልማት አጋሮች፣ የዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎችና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

# ኢንስቲትዩቱ የተገኘበትን 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር የኦዲት ጉድለት ተመላሽ እንዲያደርግ ተጠየቀ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩት በኦዲት ግኝት የታየበትን የአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ጉድለት ተመላሽ እንዲያደርግ የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ።


አቶ ክርስቲያን ታደሰ

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩት የ2013 ዓ.ም የሂሳብ የኦዲት ግኝትን ገምግሟል።

በግምገማውም ቋሚ ኮሚቴው ኢንስቲትዩቱ ፕሮፖዛል ሳያዘጋጅ ለችግኝ ተከላ በሚል ለአምስት ቀናት የተጠየቀበትና በኃላፊ የተፈቀደበትን ማስረጃ ሳያቀርብ ለውሎ አበል አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ወጪ አድርጓል። ይህን ተከትሎ በኦዲት ግኝቱ የታየውን ጉድለት ለማስተካከል ምን አይነት እርምጃ እንደወሰደ ጠይቋል ።

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ክርስቲያን ታደሰ፤ ኢንስቲትዩቱ የሕዝብን ገንዘብ መመሪያና ደንብ በማይፈቅደው መልኩ ያለ ማስረጃ ለችግኝ ተከላ በሚል ክፍያ መፈጸሙ የተደረገው ጉዞ ሕጋዊነት የማያረጋግጥ በመሆኑ ማስረጃዎቹን መያዝና ሕግና ደንብን መከተል እንደሚገባ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

የፌዴራል ኦዲተር መሥሪያ ቤት ዋና ኦዲተር መሠረት ዳምጤ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ከመንግሥት ተቋም የመጡና አድራሻ ላላቸው ሠራተኞች የተከፈለ በመሆኑ ተመላሽ ማድረግ እንደሚኖርባቸው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ኢንስቲትዩቱ ባለፉት ዓመታት ይታይበት የነበረበት የኦዲት ግኝት እያሻሻለ ነው ያሉት ኦዲተሯ፤ በተቋሙ የታዩ አብዛኛዎቹ የኦዲት ግኝቶች ሕግን በመተላለፍ የተከፈሉ ክፍያዎች ናቸው። እናም የሚከፈሉ ማንኛውም ክፍያዎች ሕግና ደንብ ተከትሎ መሆን እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል።

በኦዲት ግኝቱ ላይ ምላሽ የሰጡት የቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር ሀብቶም ገብረእግዚአብሔር እንደገለጹት፤ ክፍያው ኃላፊዎች አውቀውት የተመራ ክፍያ ነው። በወቅቱ ተቋሙ ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ ስለነበረ የሌሎች ተቋማት ሠራተኞች በችግኝ ተከላው ተሳትፈዋል። ገንዘቡ ለእነዚህ ሠራተኞች የተሰጠ አበል ነው። ይሁንና ሠራተኞቹ ከመጡበት ተቋም አበል መውሰዳቸው ከተረጋገጠ ተመላሽ እንዲያደርጉ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ የኦዲት ግኝቱን ተከትሎም የኢንስቲትዩቱ ዘጠኝ ሠራተኞች የወሰዱትን አበል ተመላሽ ማድረጋቸውን ተናግረዋል።

ቋሚ ኮሚቴው ኢንስቲትዩቱ ከመጡበት ተቋም መገባጠሚያ ሳይኖራቸውና አበል ለወሰዱ ሠራተኞች በተጨማሪነት የተከፈለው አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ተመላሽ ተደርጎ በሦስት ወራት ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር ፈሰስ እንዲያደርግ አቅጣጫ አስቀምጧል።

# ስሥራ ደህንነት ትኩረት ባለመሰጠቱ ሠራተኞች ለከፋ ጉዳት እየተጋለጡ ነው

ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- አሠሪዎች ለሥራ ላይ ደህንነትና ለጤናማ የሥራ አካባቢ ትኩረት ባለመስጠታቸው ሠራተኞች ለከፋ ጉዳትና ለበሽታ እየዳረጋቸው መሆኑን የአዲስ አበባ ሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጤናማና ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ቦታ እንዲኖር ለማስቻልና የሕጻናት የጉልበት ብዝበዛን ለመቀነስ ያለመ የፓናል ውይይት ትናንት ከባለ ድርሻ አካላት ጋር አድርጓል፡፡

በአዲስ አበባ ሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የአሠሪና ሠራተኛ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ዮሐንስ ምትኩ በፓናል ውይይቱ ወቅት እንደተናገሩት፤ አሠሪዎች ለሠራተኛው የሥራ ላይ ደህንነትና ለጤናማ የሥራ ቦታ ተገቢውን ትኩረት ባለመስጠታቸውና የግንዛቤ እጥረት በመኖሩ ምክንያት ሠራተኛው ለከፋ አደጋና ለበሽታ እየተጋለጠ ነው ፡፡

አሠሪውም ሆነ ሠራተኛው እንዲሁም በኢንዱስትሪው ማኅበረሰብ ጋር ያለው የሥራ ደህንነት የግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑ እንዲሁም የሚደርሱ ጉዳቶች በትክክል ተመዝግበው ሪፖርት ማድረግ አለመቻሉ ችግሩን አባብሶታል ያሉት አቶ ዮሐንስ፤ በተጨማሪም ለአደጋ ተጋላጭ የሥራ ሁኔታዎች እንዳይከሰቱ የሚያደርጉ አስፈላጊው የመሥሪያ ግብዓቶች ማሟላት ያለመቻል ጉዳቱ በየጊዜው እንዲከሰት ገፊ ምክንያት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ዮሐንስ ገለጻ፤ በሥራ ምክንያት በሠራተኛው ላይ የሚደርሰው የጤና ጉዳት ጫና የሚያሳድረው በሠራተኛው ላይ ብቻ የሚቆም ሳይሆን በድርጅቶችና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጭምር ነው ብለዋል፡፡

አቶ ዮሐንስ የሠራተኛው ደህንነትና ጤንነት ሳይጠበቅ ምርትና ምርታማነት ይኖራል ብሎ ማሰብ አዳጋች ነው፡፡

ለሀገሪቱም ሆነ በከተማው የኢንዱስትሪው ልማት መፋጠን ለሥራ ላይ ደህንነትና ጤንነት ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል ያሉት አቶ ዮሐንስ፤ ቤተ ሙከራዎችን በማደራጀት ለአምራች ኢንዱስትሪውና ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በጥናትና ምርምር ሥራዎች እንዲሁም የሥራ ሁኔታዎችን ልኬትን በመውሰድ ከዓለም አቀፍ መስፈርት (ስታንዳርድ) ልክ እንዲሻሻሉ ሙያዊ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ አስታውቀዋል፡፡

በፓናል ውይይቱ ወቅት በሠራተኛው ላይ በሥራ ምክንያት የሚደርሰው ጉዳት ላይ የመነሻ ሀሳብ ያቀረቡት የሙያ ደህንነትና ጤንነት የሥልጠና በለሙያ አቶ ማርቆስ አድማሱ በበኩላቸው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ 1156/2011 አንቀጽ 92 ላይ ሠራተኞች በሥራ ቦታ ደህንነታቸው ተጠብቆ የመሥራት መብት አላቸው ስላላቸው አሠሪዎች ለሠራተኞች በሥራ ቦታ ጉዳትና በሽታ እንዳይዛቸው የመከላከያ ቁሳቁስና አልባሳት የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው ያትታል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ማርቆስ ገለጻ፤ ሠራተኛው ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ለሥራው አስፈላጊውን የቁሳቁስ ግብዓት ባለመሟላቱና ተገቢውን ትኩረት ባለመሰጠቱ ምክንያት በሽታና ጉዳት በተለያየ አጋጣሚ ይደርሳል፡፡

በድርጅቶችና በአሠሪ ተቋማት የደህንነት ኮሚቴ አለመቋቋም፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አመራር ሥርዓትን ዘርግቶ ተግባራዊ ያለማድረግ በስፋት ይታያል ብለዋል፡፡

ሠራተኛው የሚሠራበት መሣሪያ ምቾት የማይሰጠው ከሆኑ ለችግሮቹ ተጋላጭ ይሆናል ያሉት አቶ ማርቆስ፣ አሠሪዎች ከሠራተኞቻቸው ተክለ ሰውነትና ቁመት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ መሣሪያ መሆን እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከዚሁ ጉዳት ጋር በተያያዘ በዓለም ኢኮኖሚ ላይ በየዓመቱ በአማካይ ከሁለት ነጥብ ስምንት ትሪሊዮን ዶላር በላይ ወጪ እንደሚደረግ በመድረኩ ተገልጿል፡፡

## «ኢፕድ ለተቋማት የሚሰጠው ሥልጠና ዋና ዓላማው...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አማካሪ ዶክተር አሸናፊ አበራ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ዓላማ ማኅበረሰባዊ ለውጥ ማምጣት ነው። ይህንን ለውጥ ለማምጣት በሥልጠና ማዕከሉ ለፌዴራልና ለክልል ተቋማት እንዲሁም ለግል ድርጅቶች በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጭ ሥልጠናዎችን በመስጠት አስመርቋል። ይህንንም አጠናክሮ ቀጥሏል።

ኢፕድ በኢትዮጵያ የሕትመት ሚዲያ የ82 ዓመት እድሜ ያለው አንጋፋ እና ስመጥር ተቋም ነው ያሉት ዶክተር አሸናፊ፤ ተቋሙ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ማኅበረሰባዊ ለውጥ ለማምጣት በሚዲያነት በርካታ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል። ኢትዮጵያም ከተቋሙ አንጋፋ ጋዜጠኞችን እና ጸሐፊዎችን አግኝታለች። አሁን ደግሞ የሥልጠና ማዕከል በማቋቋሙ ሊደነቅ እና ሊመሰገን ይገባል ብለዋል።

ማኅበረሰባዊ ለውጥ ማምጣት ተቋማዊ ለውጥ ለማምጣት ያስችላል። ይህም የኢፕድ ዓላማ ኢትዮጵያ



በሌሎች ሀገራት እንድትመሰገን እና እንድትከበር ያደርጋታል ያሉት ዶክተሩ፤ ኢፕድ በሥልጠና ማዕከሉ ተቋማት እና ሠራተኞቻቸው ያላቸውን ክህሎት እንዲያሳድጉና እንዲያሻሽሉ ሥልጠና መስጠቱ በሀገሪቱ ዘለቄታዊ ውጤት እንዲመጣ እንደሚያስችል ገልጸዋል።

ይህም ተቋማት እና ሠራተኞቻቸው አሁን ከሚሠሩት ሥራ በላይ እጥፍ ድርብ ፍሬ እንዲያፈሩ ያስችላል። ስለዚህ ተቋማት በኢፕድ የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ቢወስዱ ከተቋማዊ ለውጥ ባለፈ ማኅበረሰባዊ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ ብለዋል።

በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የትምህርትና ሥልጠና ቡድን መሪ አቶ ሡልጣን መሐመድ በበኩላቸው፤ የኢፕድ ሥልጠና ማዕከል ከዚህ በፊት ከ70 በላይ ለሚሆኑ ለፌዴራልና ለክልል ተቋማት እንዲሁም ለግል ድርጅቶች በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጭ ሥልጠናዎችን መስጠቱን ገልጸዋል።

"ማዕከሉ ያሠለጠናቸው የተቋማት አመራሮችና ሠራተኞች ተጨማሪ ሥልጠናዎችን መውሰድ እንደሚፈልጉ ይገልጹልናል" ያሉት አቶ ሡልጣን፤ በዚህም ኢፕድ ከሚዲያ ሥራው በተጨማሪ በሥልጠና ማዕከሉ የያዘውን ዓላማ ማሳካት የቻለ ሲሆን የሥልጠና ተደራሽነታችንን ከዚህም በላይ ለማስፋት በትኩረት እንሠራለን ብለዋል።

## የሱዳን የሰላም ድርድር...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ጊዜ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች።ኢትዮጵያ ለሱዳን ሰላም ስትሠራ የአሁኑ የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም።ከንጉሡ ጀምሮ በሱዳን ሰላም ዙሪያ ኢትዮጵያ ብዙ ሥራ ስትሠራ እንደነበር ገልጸዋል።

እንደ ቃል አቀባዩ ገለጻ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሁለቱን አካሎች በማገናኘት ሚና እንዲኖራቸው ተወስኗል።ብዙ የመገናኛ ብዙኃን የኢጋድ አባል አገራት ከሱዳን አንጻር የአቋም ልዩነት እንዳላቸው አድርገው የሚያሰራጩት የተሳሳተ ዘገባ ነበር፤ የጂቡቲው ስብሰባ ኢጋድ አንድ፣ ተመሳሳይና ጠንካራ አቋም መወሰዱን መረዳት ያስፈልጋል ብለዋል።ለረጅም ጊዜ የቆዩ ጉዳዮችን እልባት አበጅቷል፤ ተደራራቢ ጉዳዮችን በአንድ መደበኛ ስብሰባ ቋጭቷል፤ በመሪዎች ደረጃ የነበረው ተሳትፎ ትልቅ ነበር።በሱዳን ጉዳይ የኢጋድ አባል አገራት ተመሳሳይና ጠንካራ አቋም መያዛቸው ስብሰባው በብዙ መልኩ ስኬታማ መሆኑን ያሳያል።ሱዳናውያንን ለመታደግ የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦት ኮሪደር እንዲከፈት በመሪዎች ደረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰላምን ለማስፈን የሚያስችል ጥረት ለመጀመር ከመግባባት ተደርሷል።ኤርትራ ከረጅም ጊዜ በኋላ መመለሷ ትልቅ ትርጉም ይሰጠዋል።

ኢትዮጵያ ለኢጋድ ተልዕኮዎች መሳካትና ለተቋሙ የበለጠ መጠናከር አበክራ ትሠራለች ያሉት አምባሳደር መለስ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በስብሰባው ከመሳተፍ በተጨማሪ ከሶማሊያና ከኬንያ አቻቸው ጋር በጋራ ጉዳዮች ዙሪያና ክፍለ አህጉራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ጠቃሚ ውይይት ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

ኢጋድ ለኢትዮጵያ ትልቅ ትርጉም ያለው ተቋም ነው ያሉት አምባሳደር መለስ፤ በኢጋድ አባል አገራት መካከል ሰላምና መረጋጋት እንዲኖር፣ ክፍለ አህጉራዊ ውሕደት ለማምጣትና በአገራት መካከል ቀጣናዊ ትብብር እንዲኖር ኢጋድ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

የወቅቱ ኢጋድ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ በድጋሚ በዋና ጸሐፊነት ተመርጠዋል።ኢጋድ ባለፉት ሦስት ዓመታት በአባል አገራት ውስጥ የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት ከፍተኛ ሥራ ሠርቷል።ስብሰባው በሱዳን ብቻ ሳይሆን በደቡብ ሱዳን ሰላም እንዲመጣ ጥልቅ ውይይት ማካሄዱን አምባሳደር መለስ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የጀመረችው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር በኢጋድ አባል አገራትም የባንዲራ ፕሮጀክት ተደርጎ መወሰዱን የተናገሩት ቃል አቀባዩ፤ ከኢትዮጵያ አልፎ ክፍለ አህጉራዊና አህጉራዊ ጉዳይ ሆኗል ብለዋል ።

## «ሕዝቡ ለአብሮነቱና..

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ምክክር ከራስ ጀምሮ እስከ አገር ደረጃ የሚዘልቅ፣ የሰው ልጅም ሆነ በሰው ልጆች የሚመሩ ተቋማት በራሳቸው ሙሉ እንዳልሆኑ ግን ደግሞ ሙሉ ለመሆን ተጨማሪ ሰው ወይም ሐሳብ እንደሚያስፈልጋቸው ትልቅ ማሳያ ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ በተመሳሳይ መልኩ እንደ አገር ሰፋ ተደርጎ ሲታይም የዛሬዋ ኢትዮጵያ መልክና ቅርጽ የትናንቱ የሕዝቦቿ አስተዋፅዖ ድምር ውጤት በመሆኑ ስለነገዋም በጋራ ማጤን ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ምሕረቱ ገለጻ፣ የሰመረ የወደፊት የጋራ ጉዞ ለማድረግ ለመመካከር መወሰን እንደ ቀላል የማይታይ ምክንያታዊ ውሳኔ ነው።ምንም እንኳ ያለፉት የመንግሥት ሥርዓቶች የራሳቸው ደካማና ጠንካራ ጎን ቢኖራቸውም ስለ አገር ግን ጽኑ አቋም እንደነበራቸው እርግጠኛ መሆን ይቻላል።ከሕዝብ አንጻር ሲታይም ኢትዮጵያን ለመታደግ ያልተዋደቀ ሕዝብ አልነበረም።ሆኖም ግን መንግሥታቱ በአብሮነት ጉዞ ውስጥ የተፈጠሩ ችግሮች ላይ የመመካከር እድል ባለመስጠታቸው የዛሬ ትውልድ የድምር እዳ ተካፋይ ለመሆን ተገዷል። የምክክር ባሕልን ማዳበር ለአንድ አገር አንድነት፣ አብሮነትና እድገት ትልቅ ድርሻ መኖሩን እንደሚያሳይ ጠቅሰው፤ ከምክክር ውጪ በአገሪቱ የተሞከሩ ሌሎች የኃይል አማራጮች ከንቱ መሆናቸውን ያልተገነዘበ ኢትዮጵያዊ አለ ለማለት አያስደፍርም ብለዋል።ነገር ግን በምክክር የማይፈታ ችግር ስለሌለ ሁሉም ለምክክር መዘጋጀቱ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን አመልክተዋል።

ምክክር፣ የሐሳብ ፍጭትና ግጭት በመሆኑ ሕይወት ስለማያጠፋና ንብረትም ስለማያወድም የ21ኛው ክፍለ ዘመን ሥልጡን አካሄድ መሆኑ እጅግ ተመራጭ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በመሆኑም አገራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን በየደረጃው ያሉ አለመግባባቶች መፈታት እንዳለባቸውና ሁሉም ለምክክር ያለውን ፍላጎት ወደ ተግባር ለመቀየር የድርሻውን መወጣት ይጠበቅበታል ብለዋል።

ዛሬ በብዙ ነገሮች የማይስማማው ሕዝብ፣ ስለ ነገ አብዝቶ መጨነቁ አይቀሬ ነው።በእርግጥም ለብዙ ዘመናት አብሮ የመጣው ሕዝብ ስለነገው መጨነቁ ከአብሮነትና ከዘላቂነት የሚመነጭ ጤናማ ሥጋት ነው፤ በመሆኑም ከዚህ አንጻር የአገሪቱ መጻዒ እድል ያማረና ከሥጋት የጸዳ እንዲሆን ለምክክሩ ስኬታማነት መላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች የታላቅነት ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

በዚህ ደረጃ የምክክር መድረክን ማዘጋጀት በኢትዮጵያ የመጀመሪያ በመሆኑ ሊገጥሙት የሚችሉ ችግሮችን ለመታደግ በቁርጠኝነት መሥራት የሁሉም ኃላፊነት መሆኑም አስገንዝበዋል።

## ደረሰኝ አልባ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሬስቶራንት ውስጥ የምግብ አገልግሎት ሲጠቀሙ ያገኘናቸው አቶ ቢኒያም ያሬድ በበኩላቸው፤ ደረሰኝ መጠየቅ እንዳለባቸው እንደሚረዱ ተናግረው፣ ደረሰኝ የመጠየቅ ልምድ የለኝም ይላሉ፡፡

ብዙ ጊዜ ለገዛሁት ዕቃ ይሁን ለምገለገለው ነገር ሂሳብ ከፍዬ ነው የምሄደው የሚሉት አቶ ቢኒያም፤ ነገር ግን ለሰው የሚገዙት ዕቃ ከሆነ ለመተማመን ሲባል ደረሰኝ እንደሚጠይቁ ነው የሚናገሩት፡፡

ለሚገዙት ዕቃ ደረሰኝ የሚጠይቁት የዕቃው ዋጋ አምስት ሺህ ብር እና ከዚያ በላይ ከሆነ አልያም ለተገለገሉት ነገር የተጋነነ ዋጋ ሲጠየቁ እንደሆነ የሚናገሩት ደግሞ ወይዘሮ ዮርዳኖስ ገብረ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ደረሰኝ ሲጠይቁ ትክክለኛ ደረሰኝ የማያገኙበት አጋጣሚ እንደሚበዛ እና የእጅ በእጅ ደረሰኝ የሚባል ተፅፎ እንደሚሰጣቸው በመግለፅ በዚህም ብዙ ጊዜ አተካራ ገጥሟቸው እንደሚያውቅ ያስረዳሉ፡፡

ኢፕድ በመዲናዋ የተለያየ የንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩትን የደረሰኝ አሰጣጥ በቃኘበት ጊዜ ኮተቤ አካባቢ ላይ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩት ወይዘሮ ራሄል አሰፋ (ስማቸው የተቀየረ)፤ ደረሰኝ መቁረጥ ያቆምኩት የምጠየቀው ግብር ከፍተኛ እየሆነ በመምጣቱ ነው ይላሉ፡፡

በምከፍለው ያልተመጣጠነ ግብር ምክንያት ትርፋማ መሆን አልቻልኩም የሚሉት ወይዘሮዋ፤ በዚህ ምክንያት ደረሰኝ ሳልቆርጥ እሸጣለሁ ብለዋል፡፡

አራት ኪሎ አካባቢ የሚገኝ ሬስቶራንት የንግድ ፈቃድ ባለቤት አቶ ቢኒያም ተክሉ (ስሙ የተቀየረ) በበኩላቸው፤ በድርጅታቸው ውስጥ ያለደረሰኝ አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡

ግብር አለመክፈል ተገቢ እንዳልሆነ ባውቅም ግብር ያለመጠን እንዳልጠየቅ በመፍራት ንግድ ቤቴን ከከፈትኩ ጀምሮ ለሁለት ዓመት ያህል ያለደረሰኝ ስሠራ ቆይቻለሁ የሚሉት አቶ ቢኒያም፤ ከፍተኛ ግብር በመጠየቃቸው ምክንያት ንግድ ቤታቸውን የዘጉ እንዳሉ በማየታቸውም ይህን ለማድረግ እንዳነሳሳቸው አብራርተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ቢሮ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተወካይ አቶ እንዳለ ከበደ ከዚህ ጋር ተያይዞ በሰጡት ምላሽ፤ የደረሰኝ መስጠት እና መቀበል ችግር በስፋት እንደሚስተዋል ገልጸው፤ ኅብረተሰቡ በግብይት ጊዜ ደረሰኝ የመቀበል ልምዱ ሊዳብር እንደሚገባ እና ጥቅሙም



አቶ እንዳለ ከበደ

ለሀገር እንደሆነ መገንዘብ ተገቢ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

በተለይ እያንዳንዱ ሻጭ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት ጠቁመው፤ ቅሬታ ቢኖርበት እንኳን የቅሬታ ማቅረቢያ መንገዶች ስላሉ ከዚህ ውጭ ግብር በዛ ብሎ ያለደረሰኝ መሸጥ ሕገወጥና ቅጣት የሚስከትል እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡ የሚጣለው ግብር እንዲያውም ይበልጥ አስተማማኝ የሚሆነው ደረሰኝ በሚቆረጥበት ጊዜ እንደሚሆንም አብራርተዋል፡፡

ከግብር ጋር ተያይዞ ከንግዱ ማኅበረሰብ ለሚነሱ ጥያቄዎች እንዲሁም በጥናት የተረጋገጡ ችግሮችን ለመፍታት በአቅራቢያቸው የሚገኙ ቢሮዎችን መጠቀም እንደሚቻል የሚናገሩት ኃላፊው፤ በተጨማሪም በ16 የከተማዋ ቅርንጫፎች የቅሬታ ሰሚ አስተናጋጆች ለተገልጋዮች ክፍት ሆነው እየሠሩ እንደሚገኙ አብራርተዋል፡፡ አጭር ነፃ የሥልክ መስመር 7075 ላይ በመደወል ቅሬታን ማቅረብ እንደሚቻልም ጠቁመዋል፡፡

በመሆኑም በነጋዴው የሚነሱ ድፍን ቅሬታዎች ተገቢነት እንደሌላቸው እና በትክክለኛ መንገድ ሥርዓቱን ጠብቆ በማስረጃ ለተረጋገጠ ችግር መፍትሔ የሚሰጥ ቢሮና ሠራተኛ እንዳለ በመጥቀስ፤ ለነጋዴ ግብር መክፈል ግዴታው እንደሆነ በትኩረት ካለመረዳትና እያወቁም ጭምር ያለደረሰኝ የሚሠሩ ግለሰቦችና ተቋማት እንዳሉ ይታወቃል ብለዋል፡፡ እነዚህ አካላትም ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አሳስበዋል፡፡

ነጋዴዎች ለሚሰጡት አገልግሎት ትክክለኛ ደረሰኝ እንዲቆርጡ ተገልጋዩም ደረሰኝ በመጠየቅ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት ብለውም፤ አሁንም ተገልጋዩ ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባ እና የንግድ ሥርዓቱን ጠብቀው በማይሠሩ ነጋዴዎች ላይ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወሰድ በአፅንዖት ገልፀዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ተነጋግሮ ሀገርና ሕዝብን አሸናፊ ለሚያደርግ የሃሳብ ትግል ልንዘጋጅ ይገባል

ችግሮችን ለዘለቄታው ለመፍታትና የሰላም አየር የሞላበት ማህበረሰብ ለመፍጠር አለመግባባቶችን በውይይት እና በድርድር መፍታት ዋንኛ መፍትሄ እንደሆነ ይታመናል። የትናንት ጠባሳዎችን በይቅርታ በማከም ነገዎች የራሳቸውን ዕጣ ፈንታ መኖር እንዲችሉ እድል መስጠት የዚሁ እውነት አንድ አካል እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል።

በተለይም እንደኛ ባሉ ያደሩ ችግሮች ሁሌም ዛሬዎችን በሚናጠቁቸው ማህበረሰቦች ውስጥ፤ ችግሮችን ለዘለቄታው ለመፍታት ለውይይትና ለድርድር የተገዛ አእምሮ፤ ለይቅርታ የተከፈተ ልብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ውጪ ዘላቂ መፍትሄ ለማፈላለግ የሚደረግ የትኛውም አይነት ጥረት ትርጉም ያለው ውጤት ሊያመጣ አይችልም።

ያለፉት ትውልዶች በየዘመኑ ባጋጠሟቸው ችግሮች ዙሪያ ተወያይቶ ሁሌም ሀገርና ህዝብን አሸናፊ የሚያደርግ የፖለቲካ ባህል ማዳበር ባለመቻላቸው እስከ ዛሬዋ ድረስ፤ ችግሮችን በኃይል እና በሴራ የመፍታት አስተሳሰብ ሀገራዊውን የፖለቲካ መድረክ ተሸክሞታል። በዚህም ሀገር እና ህዝብ ሁሌም ተጎጂ የሚሆኑበት አዙሪት ውስጥ ለመኖር ተገደናል።

ከግለኝነትና ከዚህ ከሚቀዳው የገዘፈ የማንነት ግንባታ የሚመነጨው ይህ የፖለቲካ አስተሳሰብ፤ ለኃይል እና ለኃይል ብቻ ቅድሚያ መስጠቱ ፣ ዜጎች ጎራ እየለዩ በየዘመኑ ጠመንጃ አንግበው የራሳቸውን ብሩህ ነገዎች እንዲያጨልሙ አድርጓቸዋል ። የቀን ጨለማ በሚፈጥረው ግራ መጋባት እና ቁዘማ ውስጥ ፤ ተስፋ መቁረጥና ምሬት ውስጥ እንዲኖሩ አድርጓቸዋል።

በየዘመኑ ድህነትን እና ኋላቀርነትን አሸንፎ ወደቀደመው የስልጣኔ ማማ የመመለስ መሻታቸውን ትርጉም አልባ ህልም ከማድረግ አልፎ ፤ የሀገርን ብሄራዊ ክብር የሚያጎድፉ ፣ የግጭት እና የተመፅዋችነት አለም አቀፍ ትርክት ማጣፈጫ ዜማ ለመሆን ተገደዋል። ይህም በህዝባችን ዛሬዎች ላይ እየፈጠረ ያለው የስነ ልቦና ስብራት ቀላል አይደለም።

ራስ ወዳድነት ከፍያለ ደረጃ ላይ በደረሰበት ፤ እያንዳንዱ ሀገራዊ ሆነ አለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ ተጠቃሚነትን መሰረት ባደረገበት ባለንበት ዘመን ፤ ይዘነው የመጣነው ለኃይል እና ለሴራ የተገዛው የፖለቲካ አስተሳሰብ በየትኛውም መልኩ እንደ ግለሰብ /ፖቲከኞቻችንን/ ፤ እንደ ሀገር / ህዝባችንን/ ተጠቃሚ ሊያደርግ አይችልም ።ለዚህ ደግሞ የቅርብ ሀገራዊ ተሞክሮዎችን መመልከት ተገቢ ነው።

እንደሚታወቀው ባለፉት ስድስት አስርት አመታት ውስጥ የነበሩ ትውልዶች ለሀገሪቱና ለህዝቦቿ ብዙ በጎነቶችን ተመኝተዋል፡፡ ብሩህ የሆኑ ነገዎችን አልመዋል ። ለምኞትና ለህልሞቻቸውም ህይወታቸውን እስከ መስጠት የደረሰ መታመን ታይቶባቸዋል። ከፍ ያለ መስዋእትነት በመክፈልም ከቋንቋ ያለፈውን ቁርጠኝነታቸውን በተጨባጭ አሳይተዋል።

ብዙ በጎነቶችን መመኘታቸው ፤ ብሩህ የሆኑ ነገዎችን ማለማቸው ፤ ለዚህም የህይወት መስዋእትነት መክፈላቸው ብቻውን እራሳቸውንም ሆነ ሀገርና ህዝብን አላተረፈም፡፡ ለተጨማሪ የግጭትና የእልቂት ጥቁር ታሪክ ገጽ ግብአት ፣ የዜሮ ድምር ፖለቲካ ሰለባ ከመሆንም አልታደጋቸውም። ከተስፋ መቁረጥ እና ከዚሁ ከሚመነጭ የህይወት መሰላቸት አላተረፋቸውም።

የእነዚህ ሁሉ ችግሮች ማዕከል ደግሞ ልዩነቶችን በውይይት እና ለተሻለ ሃሳብ ተገዢ ሆኖ ችግሮችን የመፍታት የፖለቲካ ባህል ካለማዳበራችን የተነሳ ነው፡፡ በመሆኑም በየዘመኑ ትውልዶች እየከፈሉት ያለውን ያልተገባ ዋጋ ዛሬ ላይ ተነጋግሮ ማስቆም ያስፈልጋል። የዚህ ትውልድ ጀግንነት፤ በታሪክ ውስጥ ደምቆ የሚነበብበት ትልቁ ገድልም ይሄው ተነጋግሮ መግባባት፤ ተግባብቶም መስማማት፤ ተስማምቶም ሀገርን ከየትኛውም አይነት ተግዳሮት መታደግ መቻል ነው።

እንደ ሀገር ከግለኝነት እና ከዚህ ከሚመነጨው የገዘፈ የማንነት ግንባታ ወጥተን ሁሌም በውይይት /በመነጋገር / ሀገርና ህዝብን ተጠቃሚና አሸናፊ ወደሚያደርግ ለሃሳብ የበላይነት የተገዛ የፖለቲካ ባህል ልንሻገር ይገባል፡፡ ዜጎችንም ጎራ እየለዩ ጠመንጃ አንግበው የራሳቸውን ብሩህ ነገዎች ከሚያጨልሙባቸው የቀደሙት የጥፋት መንገዶች ልንታደጋቸው ይገባል።

ለዚህ ደግሞ መላው ህዝብ ችግሮቻችንን ቁጭ ብለን በመነጋገር ለመፍታት የተጀመሩ ሀገራዊ ጥረቶች ስኬታማ እንዲሆኑ የማይተካ ሚናውን ሊጫወት ይገባል። ፖለቲከኞቻችንም ቢሆኑ ጊዜ ካለፈበትና ትውልዶችን ብዙ ዋጋ ካስከፈለ የኃይልና የሴራ ፖለቲካ ወጥተው ፤ ቁጭ ብሎ ለመወያየት እና ከውይይት ለሚገኝ የሀገርና የህዝብ አሸናፊነት እራሳቸውን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል።

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ኢትዮጵያን የመክሰስ አባዜ-ከጥንት እስከ ዛሬ

ማኅሌት ተሾመ

ኢትዮጵያ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ያላት ግንኙነት ከክስ ያመለጠ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያውያን የምዕራቡን ዓለም ለማወቅ ከዛሬ 700 ዓመታት ጀምሮ በሰሜን አፍሪካና በኢየሩሳሌም በኩል ጉዞ አድርገዋል፡፡ በዚህ ጉዟቸው በቬነስ በኩል እያደረጉ እስከ አራጎን(ፖርቹጋል) ድረስ ይዘልቁ ነበር፡፡ ይሄንን የኢትዮጵያውያን አሰሳ ተጠቅመው ስለ ሀገሪቱ መረጃ የሰበሰቡ አካላት እነርሱም በበኩላቸው መልእክተኞችንና አሳሾችን ወደ ኢትዮጵያ ልከዋል፡፡

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን ምዕራቡን ዓለም የፈለጉበትና የምዕራቡ ዓለም ኢትዮጵያን የፈለገበት ዓላማ ተቃራኒ ነበር፡፡ የዚያ ዘመን ኢትዮጵያውያን የውጭ ፖሊሲ ‹በእኩልነትና በጋራ ትብብር ላይ የተመሠረተ፣ የጋራ ጠላትን ዒላማ ያደረገ ግንኙነት› ነበር፡፡ የምዕራቡ ዓለም ፖሊሲ ደግሞ ‹ወደ ምሥራቅ ለሚያደርገው አሰሳ ማረፊያ የሚሆነው፣ በቅኝነት የሚያዝ ሀገር ማግኘት› ነበር፡፡ ኢትዮጵያውያን ለዚህ የምዕራቡ ዓለም ግንኙነት አልተመቹም፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያውያን በራሳቸው የሚኮሩ፣ በራሳቸው የሚተዳደሩ፣ የራሳቸው የፖሊሲ ነጻነት ያላቸው መሆናቸው ለዚያ ዘመን ቅኝ ፈላጊዎች የሚዋጥ አልሆነም፡፡ ዛሬም ያለው ችግር ይሄው ነው፡፡

በዚህም የተነሣ በተደጋጋሚ የተሠነዘረውን የፊት ለፊትና ተዘዋዋሪ የቅኝ ግዛት ፍላጎት ኢትዮጵያውያን አምክነውታል፡፡ ምዕራቡ ዓለም ለዚህ የኢትዮጵያውያን መራራ ምላሽ መቅጫ አድርገው ከተጠቀመባቸው ዘመን ጠገብ ስልቶች አንዱ ሀገሪቱንና ሕዝቦቿን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መክሰስ ነበር፡፡ በንግሥት ዕሌኒ ወደ ፖርቹጋል ንጉሥ ተልኮ የሄደው አምባሳደር ማቴዎስና በዐፄ ልብነ ድንግል ተልኮ ወደ ፖርቹጋል ሄዶ የነበረው አምባሳደር ጸጋ ዘአብ የገጠማቸውም ይሄው ክስ ነው፡፡ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያንን እምነት፣ ባህልና ክብር የሚነካ፣ ገጽታቸውን የሚያበላሽ ክስ ነበር የፖርቱጋል ምሁራንና ፖለቲከኞች በአደባባይ ሲያቀርቡ የነበረው፡፡

ከዚያ በኋላም የኢትዮጵያና የምዕራቡ ግንኙነት ምርቅና ፍትፍት ሆኖ ነው የኖረው፡፡ በባሪያ ንግድ፣ በሰብአዊ መብት አያያዝ፣ በሃይማኖት ቀኖና፣ ኢትዮጵያ ስትከሰስ ኖራለች፡፡ ዐፄ ገላውዴዎስ የምዕራባውያንን ክስ ለማስተባበል ሁለት ዐዋጅ አውጥተዋል፡፡ የመጀመሪያው በ1541 ዓ.ም የወጣው የባሪያ ንግድን የተመለከተ ዐዋጅ ሲሆን፤ ሁለተኛው ‹የሃይማኖት መግለጫ› በሚል ርእስ በ1555 ዓ.ም ያወጡት መግለጫ ነበር፡፡ አውሮፓውያን ኢትዮጵያን በባሪያ ንግድ ሲከስሱ እነርሱ ግን አፍሪካውያንን በባርነት እየፈነገሉ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ አሜሪካ ይወስዱ ነበር፡፡

ኢትዮጵያውያን እንስሳትን ሳይገድሉ ይበላሉ፤ የሚኖሩት ዛፍ ላይ ነው፤ ሥራቸው እርስ በርስ መጋደል ብቻ ነው፤ ያልሠለጠኑ ስለሆኑ ልናሠለጥናቸው ይገባል፤ ዓለምም ረስቷቸው፣ ዓለምን ረስተው የሚኖሩ ናቸው፤ ወዘተ. የሚሉ ዕሴት ሰባሪ ክሶች በየዘመኑና በየመዛግብቱ ሲነዙ ኖረዋል፡፡ በተለይ ደግሞ ከዐድዋ ድል በኋላ እነዚህ ክሶች እየተባባሱ መጥተዋል። ኢትዮጵውያን ጨካኞች ስለሆኑ በኢትዮጵያ የተማረኩት የጣልያን ወታደሮች በጭካኔ ሊገደሉ ይችላሉ፤ የምርኮኛ መብታቸው አይጠበቅም፤ በቶሎ ካልደረስንላቸው በሕይወት አይተርፉም፤ የሚሉ ክሶች አውሮፓን ሞልተውት ነበር፡፡ ነገሩ ግን ከዚህ በተቃራኒው ነበር፡፡ ከዚህ በፊት በአውሮፓ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ምርኮኞቹ መብታቸው ተጠብቆ፤ ሕክምና አግኝተው፤ አንዳንዶቹም በበቅሎ ተጭነው ነው ለሀገራቸው የበቁት፡፡

የዚህን ዓይነት ክስ ከአምስት ዓመቱ የጣልያን ወረራ በኋላም ተከሥቶ ነበር፡፡ ዐርበኞች ጣልያንን ድል ማድረጋቸውን ተከትሎ እንግሊዞች በአውሮፓ ያሰሙት ክስ ‹የጣልያን ወታደሮች በዐርበኞች እጅ ከወደቁ ሊጨፈጨፉ ይችላሉ› የሚል ነበር፡፡ ይሄንንም ምክንያት አድርገው ቀድመው አዲስ አበባ ገቡ፡፡ አያሌ የጣልያንን ሀብት ዘረፉ፤ ያልቻሉትንም አወደሙ፡፡ ሀገሪቱንም ለዐሥር ዓመታት በጠባቂነት

> **ርዳታ ከሰብአዊነት በላይ ፖለቲካዊ ባሕሪው ያመዝናል። በተለይም ሀገሮች የሚሰጡት ርዳታ የፖለቲካ ግብ ማስፈጸሚያ ነው፡፡ ለዚህ ነው ርዳታ አልቀበለም ማለት ከእነዚህ ሀገሮች ጋር ወደ ግጭት የሚያስገባው፡፡ ርዳታ መስጠት ፖለቲካዊ እንደሆነው ሁሉ፤ ርዳታ ማቆምም በፖለቲካዊ ውሳኔ የሚከናወን ፖለቲካዊ ትርጉም ያለው ተግባር ነው**

ለመያዝ ሞከሩ፡፡ እንግሊዞቹ ይባስ ብለው ኢትዮጵያ የእንግሊዝ ዕዳ አለባት ብለው በአውሮፓ ክስ አሰምተው ነበር፡፡ ኢትዮጵያን ለኢትዮጵያ መንግሥት ለማስረከብ፣ ጣልያንን ለማስወጣት ላደረግነው ትግል 905ሺ ፓውንድ ሊከፈለን ይገባል አሉ፡፡ የእንግሊዝ ሶማሌ ላንድን ለጣልያን ስታስረክብ ግን አምስት ሳንቲም አልጠየቀችም ነበር፡፡

የባሩድ በርሜል የሚለውን መጽሐፍ ያነበበ የማጥላያ ክሱን ደረጃና ዘመናት መመልከት ይቻለዋል፡፡ ኢትዮጵያ ወደ ዓለም ማኅበር ለመግባት ስታመለክትና ጣልያን በወረራት ጊዜ ለዓለም ማኅበር አቤት ስትል ይሄው ክስ እየተከተላት መከራዋን አይታለች፡፡

ባለፈውም በሰሜኑ ጦርነት ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት ከ15 ጊዜ በላይ ለስብሰባ ተቀምጧል፡፡ ግብጽ ዓባይን ስትገድብ ከቁብ ያልቆጠረው ዓለም፣ ኢትዮጵያ ዓባይን መገደብ ስትጀምር ጉዳዩን የመንግሥታቱ ድርጅት አጀንዳና የምዕራቡ ዓለም የዲፕሎማሲ ክስ መጠንሰሻ አድርጎታል፡፡ በጦርነቱ ወቅት የርዳታ እህል እየተዘረፈ ላልተገባ ተግባር እየዋለ መሆኑን ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ስትናገር ነበር፡፡ ርዳታ ሰጪዎች ግን ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው አልፈውታል። ርዳታው ላልተገባ ነገር ቢውልም፣ ‹የኢትዮጵያ መንግሥት ርዳታ እንዳይገባ እየከለከለ ነው› የሚለው ክስ ነበር ጆሮ ያደነቆረው፡፡ ከ1000 በላይ ርዳታ የጫኑ መኪኖች በጦርነቱ ወቅት ትግራይ ቀርተው ነበር፡፡ በዚህ ወቅት መንግሥት መኪኖቹ እንዲመለሱ የሚያቀርበውን ጥያቄ ከመቀበል ይልቅ ‹ርዳታ ወደ ትግራይ እንዳይገባ ከልክላችኋል› የሚለውን ክስ ማጮህ ነበር የተፈለገው፡፡

እነዚህ አዝማሚያዎች አሁን ደግሞ ወደ ሌላ ምዕራፍ ተሸጋግረዋል፡፡ ኢትዮጵያን በርዳታ እህል ዝርፊያ ወደ መክሰስ፡፡ የርዳታ እህል በተለያዩ ጊዜያትና ምክንያቶች ላልተገባ ተግባር የዋለበት አጋጣሚ ተፈጥሮ ያውቃል፡፡ ችግሩ ሊፈታ የሚችለውም የተስተካከለ የርዳታ ሥርጭት አሠራር በመዘርጋትና ችግር ሲያጋጥም ሁሉን አቀፍ የሆነ ምርመራ በማድረግ ነው፡፡ ርዳታ ከሰብአዊነት በላይ ፖለቲካዊ ባሕሪው ያመዝናል፡፡ በተለይም ሀገሮች የሚሰጡት ርዳታ የፖለቲካ ግብ ማስፈጸሚያ ነው፡፡ ለዚህ ነው ርዳታ አልቀበለም ማለት ከእነዚህ ሀገሮች ጋር ወደ ግጭት የሚያስገባው፡፡ ርዳታ መስጠት ፖለቲካዊ እንደሆነው ሁሉ፤ ርዳታ ማቆምም በፖለቲካዊ ውሳኔ የሚከናወን ፖለቲካዊ ትርጉም ያለው ተግባር ነው፡፡ ርዳታን በተመለከተ የሚሰጡ መግለጫዎችም ይሄንኑ ፖለቲካዊ ፍላጎት የሚያስፈጽሙ ናቸው፡፡ በዓለም ላይ ከርዳታ ድርጅቶች ቀጥለው የምግብ ርዳታ እንዲሰጥ የሚወተውቱት የለጋሽ ሀገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች መሆናቸው የርዳታውን ፖለቲካዊ

ወደ 6ኛው ገጽ ዞሯል

# ነፃ ሃሳብ

# ኢትዮጵያን የመክሰስ ...

ከ5ኛው ገጽ የዞረ

ሚዛን የሚሳይ ነው።

ርዳታ ምን ያህል የፖለቲካ ውሳኔ ማስፈጸሚያ እንደሆነ ለማየት ኢትዮጵያና ሶማልያ ውስጥ የተከሠቱ አራት የታሪክ አጋጣሚዎችን እንመልከት። በ1970፣ በ1977፣ በ1944- 70 እና በ2012-13 ዓ.ም።

በ1969/70 ዓ.ም በኢትዮጵያ ውስጥ ርሃብ ተከስቶ ነበር። በጊዜው የነበረው የደርግ መንግሥት በሰኔ 1970 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሬዲዮ በወሎና በትግራይ 1ነጥብ5 ሰዎች ለረሃብ መጋለጣቸውንና 400 ሺህ ኩንታል ምግብ እንደሚያስፈልጋቸው ተናገረ። በአውሮፓና በአሜሪካ የነበሩ ፖለቲከኞችና የሚዲያ ሰዎች መጀመሪያ ያሰሙት ክስ ‹ውሸት ነው› የሚል ነበር። የደርግ መንግሥት የተመረተውን ምግብ ለወታደሮቹ ስላዋለው፤ የቀረውንም ለመሣሪያ መግዣ ወደ ሶቪየት ስለጫነው ነው› ተባለ። አሜሪካኖች ይሄንን የሚሉት ኢትዮጵያ የከፈለችበትን መሣሪያ አንሰጥም ብለው ካስቀሩባት በኋላ ነው። በ1971 ዓ.ም ጥቅምት ወር ኮሎኔል መንግሥቱ ራሳቸው በሚዲያ ወጥተው ችግሩ አሳሳቢ መሆኑን ገለጡ። አብዛኛው የምዕራቡ ፖለቲከኛና ሚዲያ ነገሩን ለፖለቲካ ልዩነት ማራገቢያና ከሶቪየት ጋር የነበረውን ግንኙነት ለማጠልሺያ ነበር የተጠቀመበት። ‹ኢትዮጵያ ምግብ ከገበሬው ነጥቃ ለወታደሩና ለመሣሪያ መግዣ አዋለችው› የሚል ነበር የሚሰማው ክስ።

በ1977 ዓ.ም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተለመደው ረሃብ ተከሠተ። የርሃብተኛው ብዛት እስከ አምስት ሚልዮን እንደሚደርስ፣ ከእነዚህ መካከል 700 ሺዎቹ አስቸኳይ የምግ ርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው የርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን አዲስ አበባ ለሚገኙት ኤምባሲዎች አሳወቀ። ምላሹ ግን ከተጠበቀው እጅግ ያነሰ ነበር። ፖለቲካ ዋናው ምክንያቱ ነበር። ለርሃብተኞች ከመድረስ ይልቅ የደርግን መንግሥት መክሰስና መጉዳት ዋና ዓላማ ሆነ። በዚህ ዘመን ብዙ የአፍሪካ ሀገራት ወደ ሶሻሊስት ያደሉበት ዘመን ስለነበር የአሜሪካ ርዳታ እጅግ ቀንሶ ነበር። ሐዋርድ ዎልፐ፣ ሚኪ ሊላንድ፣ ዊሊያም ኤች፣ ግሬይ የተባሉት የኮንግረስ ሰዎች እየወተወቱ፣ ጆን ዳንፎርዝን የመሰሉ ሴናተሮች እየጮኹ የሬገን አስተዳደር ግን ‹ምግብን ለፖለቲካ ዓላማ› በመጠቀም ጆሮ ዳባ ልበስ አለ። ለሚጠየቀው ጥያቄ ዋና መከራከሪያው ‹የርዳታው እህል ወደ ተረጂዎች ሳይሆን ወደ ወታደሮች ይሄዳል› የሚል ነበር። የዩኤስ ኤይድ ሁለት ሠራተኞችም ‹የርዳታ እህል እየተሸጠ ከሶቪየት ለመሣሪያ መግዣ ይውላል› የሚል ክስ አሰሙ። ከዚህ ብሶ ‹መንግሥት በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች የምግብ እጥረት የለም› ማለትም ጀመሩ። የዚህ አዝማሚያው ሌላ ነበር። ርዳታ በሌላ በኩል ይግባ ለማለት።

(እኤአ 1982) በአውሮፓ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ባለሙያዎች የተካሄደው ምርመራ ግን የአሜሪካና የእንግሊዝ መንግሥታት ክስ የተጋነነ መሆኑን አሳይቷል። በሚያዝያ 1975 ዓ.ም በርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን በኩል ታይተዋል የተባሉ የሙስናና የአስተዳደር ችግሮች ኃላፊዎችን በመቀየርና አሠራሮችን በማሻሻል ተስተካክለው ነበር። እኤአ በ1984 (1976 ዓ.ም) የዩኒሴፍ ባለሙያዎች 2000 ማይልስ ያህል በኢትዮጵያ ተዘዋውረው የተመለከቷቸውን የርዳታ ማከማቻና ማከፋፈያ ሥፍራዎች መሠረት አድርገው በሠሩት ሪፖርት፣ የሁለቱ መንግሥታት ክስ ሐሰት መሆኑን ተናግረዋል።

የአሜሪካና የእንግሊዝ መንግሥታት ለሁለት ዓመታት ርዳታን ከኢትዮጵያ በማስቀረት የሠሩት ሥራ ዓላማ የመንግሥቱ ኃይለ ማርያምን መንግሥት አስጨንቆ ለመለወጥ (regime change) የታሰበ መሆኑን በጥቅምት 1977 ዓ.ም ሬቨረንድ ቻርለስ ኤልዮት የተባሉ የክርስቲያን ርዳታ ድርጅት ዳይሬክተር ገልጠው ነበር። ‹የተባባበሰ ችግር ከተከሠተ፣ ሥርዓቱን እንደገና ሊቀይረው ይችላል ብለው አስበዋል› ሲሉ ለሳምንታዊ የእንግሊዝ ጋዜጣ ለኦብዘርቨር ተናግረው ነበር። የኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለመለወጥ የወሎ ርሃብ እንዳገለገለው ሁሉ የ77ቱን ረሃብም የመንግሥቱ ኃይለ ማርያምን መንግሥት ለመጣል እንጠቀምበት ዓይነት ነው።

በመንግሥት በተያዙ አካባቢዎች እጥረት የለም ብለው ለፖለቲካ ጥቅም ሲሉ ያመኑት ምዕራባውያን፣

> **የችግር ነጋዴዎች ከመቀሌ እስከ ሮም፣ ከጀኔቫ እስከ ኒውዮርክ በፈጠሩት ሠንሰለት እንዴት ይሄን የሐሰት ክስ እንዳራገቡት ስትሰሙ ኢትዮጵያን መክሰስ ኢትዮጵያን የመታገያ አንዱ የፖለቲካ መንገድ መሆኑን ትረዳላችሁ። "ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ" በአማራና በአፋር ክልሎች ላይ የፈጸመው ግፍ ዓላማ ኢትዮጵያን ለመክሰስ ምቹ ስላልሆነለት ነበር**

በዚህ ጊዜ በሱዳን በኩል ወደ ትግራይ ርዳታ እንዲገባ የደርግ መንግሥትን ቁም ስቅሉን አሳዩት። ደርግ በደረሰበት ጫና ምክንያት በሱዳን በኩል ርዳታ ወደ ትግራይ እንዲገባ ፈቀደ። ይህ ርዳታ ግን ብዙ መዘዝ ይዞ መጥቶ ነበር። አንዱን ብቻ በዚህ ጊዜ ማየት ተገቢ ነው። ይሄንንም በወቅቱ የነበሩት የሕወሓት ሰዎች አረጋዊ በርሄ(ዶር) እና ገብረ መድህን አርአያ በየመጽሐፎቻቸው አስፍረውታል። የርዳታ እህል ለተረጂዎች ሳይደርስ ይሸጥ ነበር። ለወታደራዊ አገልግሎት ይውል ነበር። ይሄ ሲሆን ግን የርዳታ ሰጪ ሀገሮችና ተቋማት ያውቁ ነበር። ሆኖም ዓላማቸው ደርግን መውጋት በመሆኑ ፖለቲከኞችና ሚዲያዎች በዝምታ መመልከታቸውን ገልጠውታል። ለዚህም ነው ርዳታ የፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ ነው የሚባለው። ደርግን ባደረገውም ባላደረገውም ይወቅሱ የነበሩ ምዕራባውያን፣ ዐማጽያኑን ግን ‹መሐረቡን አላየንም› ብለው አልፈዋቸዋል።

በ1964 ዓ.ም አካባቢ የአሜሪካና የሶማሊያ የጦር ግንኙነት ሲጀምር የአሜሪካ ርዳታ በዚያ ጊዜ የአሜሪካ የዓለም አቀፍ ርዳታ ኤጀንሲ(AID) በሚባለው ተቋም በኩል ሶማልያ መድረስ ጀመረ። ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር የድንበር ግጭት ስለነበራት የአሜሪካን ርዳታ ለወታደራዊ ተግባር ታውለው ነበር። የአሜሪካ ባለ ሥልጣናት ይሄን ያውቃሉ። ለጋራ ጥቅማቸው ሲሉ ግን ባላየ አልፈውታል። እኤአ በመጋቢት 1986 በጄኔራል አካውንቲንግ ቢሮ አማካኝነት ይሄ ጥፋት ተጠንቶ “Famine in Africa: Improving Emergency Food Relief Programs” በሚል ርእስ ለአሜሪካ ኮንግረስ ቀርቦ ነበር። የአሜሪካ ፖለቲከኞችና ሚዲያ ግን በቸልታ አልፎት ነበር። የዚህም ምክንያቱ ኢትዮጵያንና ሌሎች ሶሻሊስት የአፍሪካ ሀገሮችን ‹ርዳታን ላልተገባ ዓላማ አውላችኋል› በሚል ክስ ተጠምደው ስለነበረ ነው። በተለይም በ1977 ዓ.ም አካባቢ በነበረው ከባድ ድርቅ ጊዜ የርዳታ ምዝበራው ተባብሶ ነበር። ከ16 ሺህ ቶን ርዳታ መካከል 12 በመቶው ብቻ ለተራቡት ይደርስ ነበር። 9 በመቶው ለሶማሊያ ወታደሮች ሲላክ፣ 21 በመቶ ደግሞ ለሌሎች መንግሥታዊ አካላት ይደርስ ነበር። 58 በመቶ ደግሞ ፈጽሞ አይሠራጭም። ይሄን ሁሉ የአሜሪካ ፖለቲከኞችና ሚዲያዎች ‹የወዳጅ ገመና አይነገርም› ብለው አልፈውታል።

በቅርቡ በ2012 እስከ 2013 ዓ.ም በሰሜኑ ጦርነት የተከሠተውን ደግሞ የዓይን እማኙ ኦማሞ (S.E.Omamo)፣ “At The Center of the World in Ethiopia” በተሰኘው መጽሐፉ በዝርዝር ገልጦታል።

ኦማሞ፣ በጦርነቱ ጊዜ ታላላቅ "ዓለም አቀፍ ተቋማት" ሲጫወቱ የነበረውን አፍራሽ ኢትዮጵያን የመክሰስ ሚና ከገጠመኙ ተነሥቶ ይተርካል። ኦማሞ እአአ ከ2018 - 2021 መጨረሻ ድረስ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዓለም የምግብ ፕሮግራም የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ነበረ። "የትግራይ ረሃብ" የሚባለው ትርክት "በችግር ነጋዴዎች" የተፈጠረ ክስ እንደነበር ይተርክልናል። የችግር ነጋዴዎች ከመቀሌ እስከ ሮም፣ ከጀኔቫ እስከ ኒውዮርክ በፈጠሩት ሠንሰለት እንዴት ይሄን የሐሰት ክስ እንዳራገቡት ስትሰሙ ኢትዮጵያን መክሰስ ኢትዮጵያን የመታገያ አንዱ የፖለቲካ መንገድ መሆኑን ትረዳላችሁ። "ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ" በአማራና በአፋር ክልሎች ላይ የፈጸመው ግፍ ዓላማ ኢትዮጵያን ለመክሰስ ምቹ ስላልሆነለት ነበር። በእነዚህ አካባቢዎች የተፈጸመውን ግፍ በዝምታ እያለፈ በሌላ በኩል ተፈጽሟል ስለሚለው የሐሰት ክስ ሚዲያዎቹን ሁሉ ያስጮህ ነበር። ትግራይን በተመለከተ ሲወጡ የነበሩ የሞት፣ የረሃብና የችግር ሪፖርቶች እንዴት ሲቀመሩ እንደነበሩ ከመጽሐፉ ታነባላችሁ።

ስለተዘረፈ ነዳጅና እህል፣ ቀልጠው ስለ ቀሩ የርዳታ መኪኖች አንዳች እንዳይነሣ ሲደረግ ነበር። "በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ" ስም ስለ ኢትዮጵያ ሲሰጡ የነበሩ መግለጫዎች፣ ትዊቶችና ማሳሰቢያዎች ችግሩን በማያውቁና ፍላጎታቸው ኢትዮጵያን መክሰስ ብቻ በሆኑ ኃላፊዎችና የጀርባ ገፊዎቻቸው የሚመሩ መሆኑን ታረጋግጣላችሁ። በኢትዮጵያ ላይ "ታላላቅ ሀገሮች" የሚከተሉት አካሄድ ከዘረኝነት ጋር ያለውን ትሥሥር ስትረዱ ታዝናላችሁ።

እነዚህ ከላይ የተገለጡ አራት ማሳያዎች የርዳታ እህልን በተመለከተ የሚሰጡ መግለጫዎች ከመቆርቆርና ለድኾች ከማዘን የሚመነጩ ሳይሆኑ፤ ፖለቲካዊ ፍላጎትን ለማስፈጸም ከሚመነጭ ፍላጎት የሚነሡ መሆናቸውን ያሳዩናል። ኢትዮጵያን በተመለከተ ከሰሞኑ የተነሡ ክሶች በዋነት የሚመነጩት ከተፈጠሩ ስህተቶች ሳይሆን ከፖለቲካዊ ፍላጎት ነው። ነገሮቹን ነጥብ በነጥብ እንመልከታቸው።

1. የርዳታ እህል አይሰረቅም ወይ? ከተባለ፣ የርዳታ እህል ላልተገባ ተግባር ሊውል የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል። የኢትዮጵያ የርዳታ እህል ሥርጭት ከዚህ ነገር ሙሉ በሙሉ የነጻ የበቃ ነው ለማለት አያስደፍርም። አሁን ያለው ጩኸት ግን ከፍየሏ በላይ ነው። 70 በመቶው የርዳታ እህል የሚሠራጨው በራሳቸው በርዳታ ሰጪ ተቋማት በኩል ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ለተፈጠረው የሥርጭት ክፍተት 70 በመቶን ተጠያቂነት ይወስዳሉ ማለት ነው። ወይም ደግሞ ቢያንስ የርዳታ ሰጪ ተቋማት ኃላፊዎችና ሠራተኞች እጅ አለበት። ይህ ግን በፍጹም እንዲነሣ አልተፈለገም።
2. ከዚህም በተጨማሪ የርዳታ እህል ሥርጭት ላልተገባ ተግባር መዋሉን የሚያመለክት ፍንጭ ሲገኝ ርዳታው ከሚሰጥበት ሀገር የመንግሥት ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር ሁሉንም የተመለከተ ምርመራ እንዲካሄድ ይደረጋል። የኢትዮጵያ መንግሥትም ይሄን ምርመራ ከረጂ ተቋማት ጋር በጋራ ለማካሄድ ዝግጁ መሆኑን ገልጿል። ታድያ አስቀድሞ ክሱን ማጯጯህ ለምን አስፈለገ? ከዚህ በፊት በነበሩት የርዳታ ስርቆት ተግባራት ጊዜ ምርመራ ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆኑ አካላትስ አሁን ለምን ተጣደፉ?
3. በማሳያነት የሚቀርቡ ሁነቶችስ፣ ከተባለም፣ የርዳታ እህል ተሸጧል ለማለት የሚቀርቡት ሁለት ሁነቶች አጠራጣሪ ናቸው። የመጀመሪያው በገበያ ላይ መገኘቱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በወፍጮ ቤት መታየቱ ናቸው። ርዳታ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሁለት ምክንያቶች ይሰጣል። የመጀመሪያው በምግብ ለሥራ ፕሮግራም ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በቀጥታ ለተረጂዎች የሚሰጥ ነው። በሁለቱም መልኩ ርዳታው ለገበያ የሚቀርብበት ዕድል አለ። ተረጂዎች የርዳታ እህሉን ብቻ አይፈልጉትም። የርዳታ እህሉን በመሸጥ የሚገዟቸው ነገሮችም አሉ። እነዚህን ነገሮች ለመግዛት ሲሉ የርዳታ እህሉን ወደ ገበያ ያወጡታል። የወፍጮ ቤቱም ጉዳይ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነው።
4. የርዳታ ስንዴው ስርቆት ለምን ከኢትዮጵያ የስንዴ አምራችነት ጋር እንዲያያዝ ተፈለገ? የሚል ነጥብ ሊነሳ ከቻለም፣ የኢትዮጵያ የስንዴ ሉዓላዊነት ሀገሪቱን አንድ ርምጃ ወደ ላይ የሚወስዳት ነው። ኢትዮጵያ በየዓመቱ ለስንዴ ግዥ ከ710 ሚልዮን ዶላር በላይ ታወጣለች። የሀገር ውስጥ የስንዴ ፍላጎ ከ65 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ደርሷል። ከዚህ ውስጥ 70 በሙቶ በሀገር ውስጥ ሲመረት 30 በመቶው ከውጭ ይገባ ነበር። ይሄን ለማስቀረትና ራስዋን ለመቻል በበጋና በመኸር የስንዴ ልማት ላይ ተሠማርታለች። በዚህም የተነሣ ከውጭ ስንዴ በግዥ የማታስገባበት ጊዜ ላይ ደርሳለች። ይሄ ያላስደሰታቸው አካላት ገና ከመነሻው ዕንቅፋት ሲፈጥሩ ነበር። ኢትዮጵያ ምርቷን ስታበስር ወደ ኢትዮጵያ የሚላክ ስንዴ ከዩክሬይን መነሣቱን ሚዲያዎች አራገቡ። ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሀገራት ስንዴ ለመሸጥ ስትነሣ በወረደ ዋጋ እነርሱ ማቅረብ ጀመሩ። አንዳንድ ሀገራትን የኢትዮጵያን ስንዴ እንዳይገዙ ጫና አደረጉባቸው። ዛሬ ደግሞ ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የሸጠችው ስንዴ የርዳታ እህሉን ነው ተብሎ እንዲታሰብ የሚያደርግ ፕሮፓጋንዳ መንዛት ተጀመረ። የዚህ ሁሉ ዓላማ በተለመደው የኖረ ዘፈን ሀገሪቱን መክሰስ ነው።
5. ችግሩን መፍታት ወይስ ድኾችን መቅጣት፣ የሚል ከፍ ያለ የሞራል ጥያቄ ይነሳል። ምክንያቱም ሊሆን የሚገባው ችግሩ ተከስቷል ቢባል እንኳን መፍትሔው በጋራ የምርመራ ቡድን ችግሩን አጥንቶ መፍትሔ መስጠት ነው ወይስ ርዳታው የሚሰጣቸው ድኾች መቅጣት ነው፡፡ የሚል የሞራልም የአካሄድም ጉዳይ ይነሳልና ነው። ከዚህ በፊት በጦርነቱ ጊዜ ርዳታ ተገቢ ላልሆነ ተግባር እየዋለ መሆኑ ሲነገር የምዕራብ ሀገሮችና የርዳታ ድርጅቶች ምላሽ ‹በጥቂት ጥፋተኞች ምክንያት ርዳታ የሚያስፈልጋቸው ድኾች መቅጣት የለብንም› የሚል ነበር። በዚህም የተነሣ ስለ ችግሩ መስማትም ሆነ መወያየት አልፈለጉም ነበር። ከዚያ ይልቅ ‹ያልተገደበ የርዳታ ማቅረቢያ መንገድ (unhindered humanitarian access)› ይሰጠን የሚል ነበር ጫናው። ታድያ ዛሬ ምን ተከሠተ፡ ፡ ሀገሮቹ አልተቀየሩም፤ ድርጅቶቹም እነዚያው ናቸው። ምርመራውንና ርዳታው ጎን ለጎን ማድረግ አይቻልም ነበር፡፡ ውሳኔው ፖለቲካዊ ነው የሚሰኘውም ይሄው ነው።

በ1970ዎቹ አጋማሽ የአሜሪካ የእርሻ ሚኒስትር የነበረው ኧርል ቡትዝ ‹ምግብ የጦር መሣሪያ ነው፤ በመደራደሪያ ቦርሳችን ውስጥ ከሚገኙት መሠረታዊ መሣሪያዎች አንዱ ነው› ብሎ ነበር። የኤሊኖይስ ገበሬ የነበረውና በሮናልድ ሬገን የእርሻ ሚኒስትር ሆኖ የተመደበው ጆን ብሎክ እኤአ በ1980 ‹በዓለም ላይ ሰላምን ለማስፈን ከሚያስችሉን የጦር መሣሪያዎች ዋናው ምግብ ነው ብዬ አምናለሁ› ብሎ አጽንቶታል። የምግብ ርዳታ ከሰብአዊ ርዳታነቱ ይልቅ የጦር መሣሪያነቱ የበለጠ ነው። በርግጥ ርዳታን እምቢ ለማለት በሚያስችል ዐቅም ላይ ላንሆን እንችላለን። ርዳታውም የሚያስፈልጋቸው ሚሊዮኖች ወገኖች አሉን።

ከግማሽ ምዕተ ዓመት የተሻገረ የምግብ ርዳታ ታሪክም አሳልፈናል። ሆኖም ርዳታ ተረጂዎችን ከማብዛት አልፎ ያመጣልን መሠረታዊ ለውጥ የለም። የፈጠርነው የተረጂነት ባህል ግን ሉዓላዊነታችን የሚገዳደር ሆኗል። የአሜሪካ የርዳታ ድርጅት(USAID) እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራውን የጀመረው እኤአ በ1961 ነው።

በነጻነታችን እንደልብ እንዳንኮራ የሚያደርገን ተረጂነታችን ነው። ርዳታ እንዳይቀርብልን ከምናደርገው ርብርብ ይልቅ ርዳታን ለመተካት የምናደርገው ትግል ሙሉ ነጻነት ያመጣልናል። የሰሞኑ ‹እህል አንሰጣችሁም› ማስፈራሪያ ከሚያመጣብን ኀዘን ይልቅ የሚያስከትልብን ንዴት ከበለጠ እንለወጣለን። ጎንበስ ብለን ረጂዎችን ከመለመን ይልቅ ጎንበስ ብለን ምድራችንን ብንለምናት ኩራትና እራት አንድ ላይ ትሰጠናለች። ያለበለዚያ ግን እነርሱም መክሰሳቸውን አይተዉ፣ እኛም መሟገታችንን አናቆምም።

# ቅንነትን የሚሰብከው "ቅን ኢትዮጵያ"

አንተነህ ቸሬ

ቴክኖሎጂው፣ የሕይወት ሩጫው፣ የእርስ በእርስ ፉክክሩ... የበዛበት ዘመናዊው ዓለም ከቅንነት ጋር የሚስማማ ሆኖ አይታይም። ‹‹ቅንነት ሞተ፣ መተዛዘን ጠፋ ...›› የሚሉ ድምጾች ደጋግመው ይደመጣሉ። በተለይም የኢትዮጵያውያን መገለጫ ተደርገው ከሚቆጠሩት ባህርያት መካከል አንዱ የሆነው ቅንነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረና እየደከመ መሄዱ ያሳሰባቸው ኢትዮጵያውያን በዚሁ ጉዳይ ላይ አተኩሮ የሚሰራ የበጎ አድራጎት ተቋም ለማቋቋም አቅደው ተነሱ። የእነዚህ ኢትዮጵያውያን እቅድ የወለደው ‹‹ቅን ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ማኅበር›› የተሰኘው ምግባረ ሰናይ ተቋም በ2002 ዓ.ም ተመሰረተ። የሃሳቡ አፍላቂና ባለቤት አንጋፋው የሃይማኖት መምህር ዶክተር ቶሎሳ ጉዲና ናቸው።

የኢትዮጵያ ሕዝቦች የመከባበር፣ የቅን አስተሳሰብና የመደናነቅ ባህል የኑሮ ዘይቤያቸው ሆኖ እንዲሰርፅ የማየት ራዕይ ያለው ማኅበሩ፤ መከባበር፣ ቅን አስተሳሰብና መደናነቅ በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል በሁሉም ማህበረሰብ ተቀባይነት አግኝተውና ተስፋፍተው ለሀገር ዕድገትና ልማት አስተዋፅኦ እንዲኖራቸው የማድረግ ተልዕኮም አለው።

የመደናነቅና የመመስጋገን ባህልን ማዳበር የሚለው የማኅበሩ ዓላማ ‹‹የሀገራችን ኋላ ቀርነትና ድህነት ከምድራችን መካንነት የመነጨ አይደለም፣ የአስተሳሰብ ቅኝታችንም የተጓደለው ትምህርት ከማጣት የተነሳ አይደለም፣ በጉልበትም በስልጣንም አይደለም የደከምነው፤ የእነዚህ ችግሮች ምንጮች አለመተዋወቃችን፣ አለመተማመናችን፣ ተባብረን ለመስራት አለመጣራችን ነው። እርስ በእርሱ መልካም አመለካከት የሌለው ሕዝብ በእርምጃው ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል ግልፅ ነው። ትልቁ የአድናቆት ዓላማ በሰው ድካም ሳይሆን በሰው ብርታት ላይ፣ በሰው ውድቀት ሳይሆን፣ በሰው ስኬት ላይ ማተኮር ነው። ሰውን በአክብሮት እና በትህትና መነጽር፣ በምስጋና እና በአድናቆት መነጽር ማየት መቻል ለሁሉም ወገን ጠቃሚ ሲሆን ለሀገር እድገትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ይህ ሲባል ሂስ አይኖርም ማለት አይደለም። ገንቢ ሀሳብ የበለጠ እንድንበረታታ ያደርገናል እንጂ አይጎዳንም። የሚሰጠው ገንቢ ሀሳብ በቅን አመለካከት ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል። ተቀባዩም ቂም ሳይዝ በቅን ልቦና መቀበል ይኖርበታል። ገንቢ ሐሳብና ጤናማ አስተያየት መስጠትና መቀበል ለግልም ሆነ ለሀገር ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። አፍራሽና ተስፋ አስቆራጭ ዕይታና አንደበት ግን የጥፋት መሳሪያ ስለሆነ ልናስተናግደው አይገባም›› ከሚለው የዶክተር ቶሎሳ ጉዲና ሃሳብ የመነጨ ነው።

እንደማኅበሩ እምነት፤ ቅንነት ሦስት አምዶች (Pillars) አሉት፡- በጎ አስተሳሰብ፣ መከባበር እና መደናነቅ። ማኅበሩ እነዚህን አምዶች በማጠንከርና በማስፋፋት ቅንነት የኅብረተሰቡ መገለጫና ባህል እንዲሆንና ዜጎች በሀገር ግንባታ ላይ አዎንታዊ ሚና እንዲኖራቸው ለማድረግ ይሰራል። ከዚህ በተጨማሪም ራስንና ሌሎችን የመቀበል እሳቤ ለጠንካራና ጤነኛ ኅብረተሰብ ግንባታ ቀዳሚ እርምጃ መሆን አለበት።

የ‹‹ቅን ኢትዮጵያ›› የበጎ አድራጎት ማኅበር ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ተፈራ ሥዩም እንደሚናገሩት፣ ማኅበሩ በሀገሪቱ ያሉትን የአስተሳሰብ ክፍተቶች፣ በተለይም የቅንነት ጉድለቶችን፣ ለመሙላት ታስቦ የተመሰረተ ነው። የማኅበሩ ምስረታ በኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ የመጣውን የቅንነት ባህርይ ለማነቃቃት የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች አካል ነው።

አቶ ተፈራ ስለማኅበሩ አመሰራረትና የመጀመሪያ የሥራ እንቅስቃሴዎች ሲያስታውሱ ‹‹ቅንነት እንዲፈጠር አጋዥ የሚሆነው የመደናነቅ ባህል በኢትዮጵያ ያልተለመደ በመሆኑ ይህን ባህል እንዴት ማስፋፋት እንደሚቻል ለማመልከት አንድ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ነበር። ጥናቱን ሰባት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን እንዲያካሂዱት ከተደረገ በኋላ የተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት እና የአፍሪካ ኅብረትን ጨምሮ የልዩ ልዩ ድርጅቶች ተወካዮች፣ የመንግሥት ባለስልጣናት እንዲሁም ታዋቂ ግለሰቦች በተገኙበት ጥናቱ ቀረበ። በጥናቱ ግኝቶች ላይ በመመርኮዝ የመደናነቅ ባህሉን ወደ ቅንነት ማሸጋገር አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበት ቅንነትን የመስበክና የማስተማር ጥረቶች ቀጠለ›› ሲሉ ያብራራሉ።

በኢትዮጵያ የመደናነቅ፣ የመተባበርና የበጎ አሳቢነት ባህል እንዲዳብር በማሰብ የተመሰረተው ‹‹ቅን ኢትዮጵያ›› የበጎ አድራጎት ማኅበር፣ ይህን ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን መቆየቱን ዋና ስራ አስኪያጁ አቶ ሥዩም ይገልፃሉ። ማህበሩ ኅብረተሰቡ ስለቅንነት፣ መደናነቅና መመሰጋገን የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን አዘጋጅቷል። በእነዚህ መድረኮች ላይ ታዋቂ ሰዎችና ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅ የሆኑ አካላትን በማሳተፍ ስለቅንነት፣ አድናቆትና ምስጋና መልዕክቶች እንዲተላለፉ ያደርጋል። በየዓመቱ የግንቦት ወር የመጀመሪያው ማክሰኞ ሀገር አቀፍ የወላጆች፣ የመምህራንና የተማሪዎች የመከባበር ቀን ሆኖ እንዲከበር ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርሞ ይኸው ኹነት በየዓመቱ እየተከናወነ ይገኛል። በትምህርት ቤቶች ውስጥ የምስጋናና አድናቆት መድረኮችን በማዘጋጀት ተማሪዎች፣ ወላጆችና መምህራን እርስበርስ እንዲሞጋገሱና እንዲመሰጋገኑ ያደርጋል።

ኢትዮጵያ ሁሉም ሀብት ቢኖራትም በቅንነት ጉድለት ምክንያት ለብዙ ችግሮች ተዳርጋለች ብሎ የሚያምነው ማኅበሩ፣ ልጆች በቅንነት በተቃኘ አስተሳሰብ እንዲያድጉ ለወላጆችና ለልጆች የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ያዘጋጃል። ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በጅማ፣ በሀዋሳ፣ በድሬዳዋ፣ በአዳማና በሌሎች ከተሞች መሰል መድረኮችን የማዘጋጀት እቅድ አለው።

ማኅበሩ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ፣ አሽከርካሪዎች በቅንነት እንዲያሽከርክሩ፣ እውቀታቸውንና ችሎታ ቸውን በቅንነት እንዲጠቀሙ ያስተምራል። ቅንነትን የተላበሰ ዜጋ በማፍራት ሰላሟ የተጠበቀች ሀገር ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ከሰላም ሚኒስቴር ጋር በትብብር ይሰራል።

**በሀገራችን በሁሉም ዘርፎች ጎልቶ የሚታየው የቅንነት ማጣት ችግር እንደ ኢትዮጵያዊ ቁጭ ብለን ተነጋግረንና ተደማምጠን ለሀገራችን የሚበጀውን በጋራ ለማድረግ እንድንችል ያስገድደናል። አንዱ ተናግሮ እስከሚጨርስ ድረስ እንኳ አንጠብቅም። ብዙ አለመግባባቶች የሚፈጠሩት ባለመደማመጥ ምክንያት ነው። ይህ አለመደማመጥ ደግሞ ከቅንነት ማነስ የመነጨ ሊሆን ይችላል**

አቶ ተፈራ እንደሚሉት፣ ‹‹ቅን ኢትዮጵያ›› እስካሁን ድረስ ባከናወናቸው ተግባራት የቅንነት ባህል መሻሻል እያሳየ ይገኛል። ‹‹የዜግነት ግዴታችንን ለመወጣት ባደረግነው ጥረት ብዙ ግለሰቦችና ቡድኖች ሃሳባችንን መደገፋቸው፤ በየደረጃው ያሉ የመንግሥት አካላት ሃሳቡን እንዲረዱት ማድረጋችን እንዲሁም የቅንነት፣ የመመሰጋገንና የመደናነቅ ባህል የብዙ ሰዎች የሕይወት መገለጫ ባህርይ ሆኖ መመልከታችን በዋጋ እንደማይተመን ትልቅ ሽልማትና እውቅና እንቆጥረዋለን። የሰዎች ባህርይ በመልካምነት ተለውጦ ቅንነትን መገለጫው ያደረገ ማኅበረሰብ እውን ማድረግ ትልቅ ስኬት ነው›› በማለት የማኅበሩ ተግባራት ለውጥ ማስመዝገባቸውን ይገልፃሉ።

ማኅበሩ እንዲመሰረት ምክንያት የሆኑት አንጋፋው የሃይማኖት መምህር ዶክተር ቶሎሳ ጉዲና ሦስተኛው ሀገራዊ የማመስገንና የመደናነቅ ቀን ሲከበር ባስተላለፉት መልዕክት፤ ‹‹መመሰጋገን፣ መከባበርና መተባበር አንድነታችንን ይበልጥ ያጠናክራል፤ ቅንነትን ያዳብራል›› ሲሉ ገልጸዋል።

ሕፃናት የነገ አገር ተረካቢ ዜጎች በመሆናቸው ወላጆች፣ መምህራንና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት እነዚህ ሕጻናት ከመለያየትና ዘረኝነት ርቀው የአመስጋኝነት፣ የመደናነቅና የቅንነት መልካም እሴቶችን ተላብሰው እንዲያድጉ መተባበር እንዳለባቸው ተናግረዋል። ልጆችን በፍቅርና በስርዓት በማሳደግ ቅን ዜጎች እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመው፣ ልጆች የአሉታዊ አመለካከት መሳሪያ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባም መክረዋል።

‹‹የአንድን ሀገር ዕይታ ለመቀየር የሕዝቡን አስተሳሰብ መቀየር አስፈላጊ ነው። የሕዝብን አስተሳሰብ ለመቀየር ደግሞ ቅን አመለካከት፣ ቅን አገላለጽ፣ በጎ ሕሊናና፣ ጤናማ መንፈስ ማስፈለጉ ጥያቄ የለውም። ቅንነት የአንድ ግለሰብ እና ኅብረተሰብ ጤናማ መገለጫ ነው። የመደናነቅ ባህል በሰፊው ባልታወቀበት ምድር ዘለቄታዊ ትምህርት መስጠት የሚያመጣው የአስተሳሰብ ለውጥ የሚያስከትለው ይቅርታ፣ ዕርቅ፣ መከባበርና መተማመን በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ሁሉንም ከፍና ዝቅ ሳናደርግ የሰው ልጅን በመልካም ቃልና በሞራል ብናበረታታ የእድገታችን ምዕራፍ ቀዳሚ ይሆናል። በቤተሰብ ደረጃ ያለውን የመከባበር፣ የመደናነቅና መልካም የማሰብ ባህል ወደ ጎረቤት፣ በጎረቤት ያለውን በከተማ፣ በከተማ ያለውን በሀገር ደረጃ እናሳድግ፤ ይህም ዘላቂነት እንዲኖረው መልዕክቱን በትምህርት ቤትና በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት እናሰራጭ። በአጠቃላይ የመደናነቅ፣ የመከባበርና የቀና አስተሳሰብ ባህልን በመላው ኢትዮጵያ በተቀናጀ መልኩ በስራ እንተርጉም›› ብለዋል።

ቅንነት እየተዳከመ ባለበት ወቅት ቅንነትን ለማጎልበት የሚከናወኑ ተግባራት ብዙ መሰናክሎች እንደሚያጋጥሟቸው መገመት ከባድ አይሆንም። ‹‹ቅን ኢትዮጵያ›› ስላጋጠሙት ችግሮች አቶ ተፈራ እንዲህ በማለት ያብራራሉ፡- ‹‹ሁላችንም እንደምንረዳው በአሁኑ ወቅት ትልቅ የቅንነት ችግር አለ። ‹ቅን ኢትዮጵያ› በ2002 ዓ.ም ቢመሰረትም ለ10 ዓመታት ያህል ይዟቸው የተነሳቸውን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉትን ስራዎች እንዳይሰራ ብዙ መሰናክሎች ተፈጥረውበት ቆይቷል። የማኅበሩ ፈቃድ እንዳይታደስ እንዲሁም ‹ለመሆኑ ‹ቅን ኢትዮጵያ› ማለት ምን ማለት ነው?› እየተባለ አላስፈላጊ ለሆኑ ትርጓሜዎች እንዲጋለጥ ሲደረግም ነበር። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው በየደረጃው ያለውን የቅንነት ማጣት ችግር ነው።›› ይላሉ። ከዚህ አስቸጋሪና አላስፈላጊ ሁኔታ ውስጥ ለመውጣት በመገናኛ ብዙኃንና በኪነ-ጥበባዊ መሰናዶዎች በኩል ለሕዝቡ ተደራሽ መሆን አስፈላጊ እንደሆነ ይመክራሉ። መከባበር፣ መደናነቅና መልካም አስተሳሰብ በሰዎች ልብ ውስጥ ካሉ፤ የጠፉ ነገሮችንም መልሶ ማምጣትና ማዳበር እንደሚቻልም ይገልፃሉ።

‹‹በሀገራችን በሁሉም ዘርፎች ጎልቶ የሚታየው የቅንነት ማጣት ችግር እንደ ኢትዮጵያዊ ቁጭ ብለን ተነጋግረንና ተደማምጠን ለሀገራችን የሚበጀውን በጋራ ለማድረግ እንድንችል ያስገድደናል። አንዱ ተናግሮ እስከሚጨርስ ድረስ እንኳ አንጠብቅም። ብዙ አለመግባባቶች የሚፈጠሩት ባለመደማመጥ ምክንያት ነው። ይህ አለመደማመጥ ደግሞ ከቅንነት ማነስ የመነጨ ሊሆን ይችላል። ይህ ዓይነቱ ባህርይ የኅብረተሰባችን ባህል ሆኖ እንዳይቀጥል ስለቅንነት መነጋገርና በቅንነት መጓዝ ይገባል›› ይላሉ።

‹‹በአሁኑ ወቅት በብዙ ትምህርት ቤቶች የጀመርናቸው ስራዎች አሉ። በየትምህርት ቤቶቹ የቅንነት ክበባትን በማቋቋም ተማሪዎች ቅንነትን ባህል አድርገው እንዲያድጉ እየሰራን ነው። ይህ ስራ በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ተጀምሯል። በቀጣይም አቅም በፈቀደ መጠን ይህን ተግባር በሌሎች ትምህርት ቤቶች ለማስፋት ጥረት ይደረጋል። የስነ ምግባርና የግብረ ገብነት ትምህርት በስርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካትቶ እንዲሰጥ ማኅበሩ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል። የተማሪዎች የመመሰጋገንና የመደናነቅ ቀን ሲከበር ቆይቷል። በቀጣይ ጊዜ ይህ በመምህራንና በተማሪዎች ብቻ ተወስኖ የሚገኘው ኹነት በሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል እንዲተገበር ‹‹ሀገር አቀፍ የመመሰጋገንና የመደናነቅ ቀን›› በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አማካኝነት እንዲታወጅ ጥረት ያደርጋል። የመልካም አስተሳሰብ፣ የመደናነቅና የመመሰጋገን ባህሎች በሁሉም ተቋማትና የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲለመዱ በግንዛቤ ማስጨበጫና በሌሎች ዘዴዎች አማካኝነት የተጀመሩ ጥረቶችን አጠናክሮ ያስቀጥላል›› በማለት ስለማኅበሩ ቀጣይ እቅዶች ገልጸዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ወጣት የስነጥበብ ባለሙያ

**ክብረአብ በላቸው**

ወጣት ባዩ እምቢዓለው ይባላል። ተወልዶ ያደገው በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን ሞጣ ከተማ ነው። የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በዛው በትውልድ አካባቢው ተከታትሏል፡፡ በትምህርቱ መካከለኛ ከሚባሉ ተማሪዎች የሚመደብ እንደሆነ የሚናገረው ወጣት ባዩ ነገር ግን በወቅቱ በነበረው የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ውጤት ስላልመጣለት በማታ የትምህርት ክፍለ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሶሾሎጂ እና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ትምህርቱን ተከታትሎ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቋል።

በወቅቱ ከመደበኛ ትምህርቱ ጎን ለጎን በዛው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነ ጥበብ እና ዲዛይን ትምህርት ክፍል ተወዳድሮ በመግባት በ2001 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪ በቅርፅ ጥበብ ሁለተኛ ዲግሪውን ደግሞ በአርት ቲኦር በ2009 ዓ.ም ተቀብሏል። ወጣት ባዩ በተመሳሳይ ጊዜ በተለያየ የትምህርት አይነት ሁለት ዲግሪ ማግኘት ችሏል።

ወጣት ባዩ ወደኋላ ተመልሶ ዩኒቨርሲቲ ቆይታውን ሲያስታውስ ከተለያየ የሀገሪቱ አካባቢ የመጡ ወጣቶች ያሉበት እንደመሆኑ ትንሿን ኢትዮጵያ ማየት የቻለበት ወቅት እንደነበር ያስታውሳል፡፡ የተለያየ ሃይማኖት፣ ባህል፣ ቋንቋ እና አመለካከት ያለው ሰው በአንድ ላይ ሆኖ የሚኖርበት እና ዓላማውን ለማሳካት ሁሉም የሚጥርበት ቦታ እንደሆነ እና ደስ የሚል ቆይታ ያሳለፈበት እንደነበር ያስረዳል።

የስዕል እና ቅርፃ ቅርፅ ጥበብ ጅማሮው እንዴት እንደነበር ወጣት ባዩ ሲናገር ወደ ልጅነት ጊዜው ተመልሶ ያስታውሳል፤ አጎቱ መጽሐፍ አንባቢ እንደነበሩ እና ታዋቂ የነበሩ ግለሰቦችን ማለትም ካርል ማርክስ፣ ሌኒን እና ሌሎች መሰል የወቅቱ ታወቂ ሰዎች መጽሐፍት፣ ፎቶ እና ስዕል በቤታቸው እንደነበረ እሱም ምስሎቹን ይወዳቸው ስለነበር በተደጋጋሚ በትክክል ኮፒ እያደረገ ይስላቸው እንደነበረ ይገልጻል።

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ እንደመሆኑ በልጅነቱ እምነቱን የሚገልፁ የማሪያም እና መልዓክትን ስዕሎች በተደጋጋሚ ይሰራ ነበር፡፡ በወቅቱ በትምህርት ጥሩ እንቅስቃሴ ያሳይ ስለነበር ታላቅ ወንድሙ የስዕል ሥራውን እንዲተው እና ትምህርቱ ላይ ብቻ እንዲያተኩር እንዳደረገው እና ለተወሰነ ጊዜ የስዕል ሥራውን አቁሞ እንደነበረ የሚነገረው ወጣት ባዩ የስዕል ፍላጎቱ እና ተስጥኦ በውስጡ ስለነበር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ሲጀምር የስዕል ሥራውን ዳግም መስራት እንደጀመረ ወጣት ባዩ ይነገራል።

በወቅቱ በትንንሽ ወረቀቶች እና ሸራ ላይ የተለያዩ ስዕሎችን በተለይ መንፈሳዊ ይዘት ያላቸውን ሥራዎች እየሰራ መንገድ ላይ በመሸጥ ገቢ ማግኘት እንደጀመረ ይገልፃል፡፡ በ1995 ዓ.ም ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚያስገባው ውጤት ሳይመጣለት ሲቀር ለአንድ ዓመት በትውልድ ስፍራው እንዳሳለፈ እና ይህም ለስዕል ሥራው ሰፊ ጊዜ ለማግኘት መልካም አጋጣሚ እንደፈጠረለት የሚገልፀው ወጣቱ በዛው ዓመት መደበኛ ባልሆነ መንገድ ትምህርቱን ለመከታተል አዲስ አበባ እንደመጣ እና በዛው ወቅትም ቢሆን ከትምህርቱ ጎን ለጎን የስዕል ሥራውን ከመስራት እንዳልተቆጠበ ይነገራል።

በ1998 ዓ.ም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነ ጥበብ እና ዲዛይን ትምህርት ቤት በዘርፉ ፍላጎት ያላቸውን ልጆች ተቀብሎ ለማስተማር በወጣው ማስታወቂያ መሰራት ተመዝግቦ በአምስት ዙር የተሰጠውን የመግቢያ ፈተና በብቃት በማለፍ ትምህርቱን መከታተል እንደቻለ እና ይህም የስዕል እና ቅርፃ ቅርፅ ሥራው በተሻለ እውቀት እና መረዳት መሥራት እንዲችል እንደረዳው ወጣት ባዩ ይገልፃል።

መጀመሪያ አካባቢ የሙያውን ፍላጎት ብቻ ይዞ እንደተነሳ እና ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተቀላቅሎ ሙያውን መማር መቻሉ የሙያውን ሳይንስ መረዳት እንዲችል መልካም አጋጣሚ እንደፈጠረለት የሚናገረው ወጣት ባዩ ስዕል የገቢ ምንጭ ሆኖ እያገለገለው እንደሆነ እና በአሁኑ ወቅት ቤተሰቡንም የሚያስተዳድረው ከዚሁ ከስነጥበብ ሥራ በሚያገኘው ገቢ እንደሆነ ተነግሯል።

ስነጥበብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችን አካል ነው የሚለው ወጣቱ የምንለብሰው ልብስ፣ ቀለም፣ ሁሉ



**ወጣት ባዩ እምቢዓለው፣**

የስነጥበብ አካል ነው። ስነጥበብ አሁን አድጎ በግራፊክስ ዲዛይን እና አርክቴክቸር በመደገፍ ትልቅ የገንዘብ ምንጭ እየሆነ መጥቷል። በሌሎች ሀገራት በሚሊዮን ዶላር ስዕሎች ይሸጣሉ እኛ ሀገርም አሁን አሁን ገበያው እየተነቃቃ መምጣቱንና እስከ አንድ ሚሊዮን ብር ድረስ ስዕሎች ይሸጣሉ የሚለው ወጣት ባዩ በኢትዮጵያ ደረጃም ቢሆን ሕዝቡ ለስዕል ያለው ዝቅ ያለ አመለካከት እየተሻሻለ መምጣቱን ይናገራል፡፡ ለሆቴሎች፣ ለሎጆች፣ ለመኖሪያ ቤት ሰዎች የስነጥበብ ውጤቶችን ይገዛሉ ይህም ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ሆኗል ይላል።

ስዕል ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ባሻገር በራሱ ፍልስፍና ሀሳብ እና ስሜትን የመግለጫ መንገድ ነው የሚለው የስነጥበብ ባለሙያው ወጣት ባዩ ሰው ያደገበትን፣ የኖረበትን፣ አስተሳሰቡን፣ ባህሉን በስነጥበብ መግለጽ እንደሚቻል ያብራራል፡፡ ኢትዮጵያ በርካታ የስነጥበብ መገለጫዎች እንዳሏትና የአክሱም ሃውልቶች፤ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት፤ የፋሲል እና የሀረር የግንብ ጥበቦች ሁሉ የቅርፅ ውጤቶች ሁሉ የሰው ልጅ የተጠበባቸው ውጤቶች መሆናቸውን ይናገራል።

ሰዓሊው እንደሚናገረው በንጉሡ ጊዜ በስዕል እና ቅርፃ ቅርፅ የንጉሳዊ ቤተሰብ በሚገልጽ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በዘመነ ደርግ ከአብዮቱ ጋር የተያያዙ ስዕሎች ይሰሩ እንደነበር ከዛ በኋላ በነበረው መንግስት የስነጥበብ ዘርፉ ተዳክሞ ቆይቷል፡፡ አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ለቱሪዝም ዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶ ፓርኮች፣ መዝናኛ ማዕከላት እየተሰሩ የስዕል ኤግዚቢሽኖች ይዘጋጃሉ፤ ይህ ለኢንዱስትሪው ትርጉሙ ከፍ ያለ ነው።

ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት ሁኔታ ምስቅልቅል ቢሆንም ይህንን ችግር ስነጥበብን ተጠቅሞ ማለፍ እንደሚቻል ያምናል፡፡ ኢትዮጵያ በርካታ ባህሎችና የእርስ በእርስ መስተጋብሮች የሚታይባት ሀገር ነች፡፡ ከልዩነት ይልቅ አንድነት፤ ከመለያየት ይልቅ አብሮነት የሚታይባት ድንቅ ሀገር ነች፡፡ ይሄ በአግባቡ በጥበት አልተገለጸም፡፡ አሁን በየማህበራዊ ሚዲያው የሚገለጸው የሚያራርቁና የሚያጣሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ይሄ ደግሞ ኢትዮጵያውያንን አይገልጽም፡፡ ኢትዮጵያውያንን የሚገልጸው አብሮነት፤ አንድነት፤ ጀግንነት እና የሀገር ፍቅር ነው፡፡

ስለዚህም እነዚህን ውድ ዕሴቶች በስነጥበቡ አማካኝነት በአግባቡ አዲሱ ትውልድ ጋር መድረስ አለባቸው፡፡ አዲሱ ትውልድ ሲነገረው በነበረው መጥፎ ትርክት ሀገሩን በአግባቡ መረዳት አልቻለም፡፡ ስለዚህም በስነጥበቡ ዘርፍ የተሰማሩ አካላት የኢትዮጵያን ማንነትና ዕሴቶች በአግባቡ ወጣቱ ጋር እንዲደርስ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም የሀገራችንን መልካም ዕሴቶች እና ውብ የተፈጥሮ ስጦታዎች በጥበብ አማካኝነት ለውጭው ዓለም ማሳየት የስነጥበብ ባለሙያው የሙያ ድርሻ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ተነግሮ የማያልቅ ታሪክ፣ ባህል፣ ወግና ውብ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት ነች፡፡ የሰው ልጅ መገኛ፤ አመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች ባለቤትና የድንቅ አራዊትና አዕዋፍ መገኛ ሀገር ነች፡፡ ይህ ለስነጥበቡ ትልቅ መነሻ ነው፡፡ እነዚህን ውብ ዕሴቶች በማስተዋወቅ ብቻ ከራስ አልፎ ለሀገር መድህን መሆን ይቻላል፡፡

ሆኖም ባለፉት አመታት ለስነጥበብ ትኩረት በመነፈጉና ወጣቱም ሞራሉ እንዲላሽቅ በመደረጉ ሀገሩን በቅርብ ማየት አልቻለም፡፡ ስለዚህም ወጣቱ አይኑን ከፍቶ የሀገሪቱን ውብ ገጽታ እንዲመለከት፤ እንደ አባቶቹና ቅድመ አያቶቹ በጋራ መኖርን ባህሉ አድርጎ ኢትዮጵያን እንዲያሻግር ለጥበብ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ማንም ሰው በተፈጥሮ አንዳች አይነት የጥበብ ተስጥኦ አለው የሚለው ወጣት ባዩ፤ ብዙ ወጣቶች ሰዓሊ የመሆን ፍላጎት እንዳላቸውና ነገር የተመቻቸ ሁኔታ እና በአጋጣሚ ባለማግኘታቸው ተሰጥኦዋቸው ተቀብሮ ይቀራል፡፡

ወጣት ባዩ እንደሚለውም ወደ ሙያው የሚቀላቀሉት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተስጥኦ ያላቸውን ልጆች ትኩረት ሰጥቶ ሁኔታዎች ቀላል የሚያደርግላቸው የለም፡፡ ይህ በመሆኑ ችሎታ እና ተስጥኦው ያላቸው ልጆች እዛው ተቀብረው ይቀራሉ፡፡ ይህ እንዳይቀጥል የሚመለከተው አካል በትኩረት ቢሰራ መልካም ነው ይላል።

በልጅነት የነበረውን ሁኔታ ወጣት ባዩ ወደኋላ ተመልሶ ሲያስታውስ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ በነበረበት ወቅት የስዕል ትምህርት ይሰጥ ነበር፡፡ በየትምህርት ቤቶቹ የስዕል ማዕከላት እና ክበቦች ነበሩ፡፡ እነዚህን በመቀላቀል እና በመጠቀም ተስጥኦውን ማዳበር እንደቻለ እና አሁን ላይ በትምህርት ስርዓቱ ይህ አይነት አሰራር አለመኖሩ ዘርፉን እንደጎዳው ነገር ግን ከልጅነት ጀምሮ በህፃናት ብሎም በወጣቶች ላይ መስራት ከተቻለ እንደ ሀገር ብዙ አፈወርቅ ተክሌዎችን ማፍራት እና የኢትዮጵያን ስነጥበብ ወደፊት ማራመድ እንደሚቻል ያለውን እምነት ይገልጻል።

ስነጥበብ ካደገ የፋሽን ዲዛይኑ ያድጋል፣ አርክቴክቸሩ ወይም የህንፃ ጥበቡ ያድጋል አስተሳሰብ አብሮ ያድጋል፤ ለወጣቱ የሥራ ዕድል ይፈጠራል የሚለው ወጣቱ፤ መዋያቸውን ለራሳቸውም ለሀገራቸውም ጥቅም በማይሰጥ አልባሌ ቦታ ያደረጉ ወጣቶች እና ታዳጊ ልጆች ከጥፋት እንዲድኑ ብሎም አቅማቸውን ማውጣት እንዲችሉ የሚያግዛቸው አካል መኖር እንዳለበትና ወጣት ተኮር የሆኑ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንደ ሀገር መስፋፋት አለባቸው ይላል።

> ስነጥበብ ካደገ የፋሽን ዲዛይኑ ያድጋል፣ አርክቴክቸሩ ወይም የህንፃ ጥበቡ ያድጋል አስተሳሰብ አብሮ ያድጋል፤ ለወጣቱ የሥራ ዕድል ይፈጠራል የሚለው ወጣቱ፤ መዋያቸውን ለራሳቸውም ለሀገራቸውም ጥቅም በማይሰጥ አልባሌ ቦታ ያደረጉ ወጣቶች እና ታዳጊ ልጆች ከጥፋት እንዲድኑ ብሎም አቅማቸውን ማውጣት እንዲችሉ የሚያግዛቸው አካል መኖር እንዳለበትና ወጣት ተኮር የሆኑ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንደ ሀገር መስፋፋት አለባቸው

ዘመኑ ሁሉንም ነገር በቀላሉ በእጃችን ማግኘት የምንችልበት የቴክኖሎጂ ዘመን ነው። ተስጥኦ እና ፍላጎቱ ያላቸው ወጣቶች የግድ ትምህርት ቤት ሄደው መማር ሳይጠበቅባቸው የፈለጉትን የስነጥበብ አይነት ማወቅ እና ማየት ይችላሉ፤ በዚህም ጥበቡን በእርሳቸው መንገድ በመቀየር ተስጥኦቸውን ወደፊት ማምጣት እና ማሳደግ እንደሚችሉ ይገልፃል።

አሁን ላይ ለስዕል ሥራው የቦታ ጥበት እንቅፋት እንደሆነበት የሚነገረው ወጣት ባዩ ነገር ግን የተለያዩ አማራጮችን ተጠቅሞ በመሥራት ታዋቂ ሰዓሊ የመሆን ህልሙን መሳካት እንደሚፈልግ እና ሀገሩን በስነጥበቡ ዘርፍ በዓለም አቀፍ መድረክ ማስጠራት እንደሚፈልግ ይናገራል፡፡ ብሎም ዓለም አቀፍ የስዕል ኤግዚቢሽኖች ላይ ተሳትፎ የስዕል ሥራዎቹን ማቅረብ ማሳካት የሚፈልገው ህልሙ እንደሆነ እና ከፈጣሪ ጋር ይሳካል ብሎ እንደሚያምን ተነግሯል።

አሁን ዓለም የውድድር መድረክ ናት፡፡ ዘመኑ የጥሎ ማለፍ ነው፡፡ ወጣቱ ያንን ተረድቶ ለጊዜያዊ ስሜት እራሱን ማስገዛት ሳይጠበቅበት ሀገሩን የሚያውቅ እና የሚጠቅም አንባቢ ትውልድ እንዲሆን እና በስነጥበቡ ብቻ ሳይሆን በሳይንስ፤ በቴክኖሎጂ ላይ በመሥራት ትኩስ ጉልበቱን ተጠቅሞ ሀገሩን ለመቀየር እና ከድህነት ለማላቀቅ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ እንዳለበት ገልጿል።

ሕይወት ፈተናዋ ብዙ ነው የሚለው ወጣት ባዩ ዓላማ እስካላቸው ድረስ ወጣቶች ለዓላማቸው መሳካት መክፈል ያለባቸውን መስዋዕትነት ሁሉ መክፈል ይኖርባቸዋል። የነገው ራዕያቸውን ከግብ ለመድረስ ቀን እና ሌሊት ሳይሉ እና ተስፋ ሳይቆርጡ መትጋት እንደሚገባቸው እና በርካታ መሰናክሎች ቢኖሩም ነገን አሻግሮ መመልከት እንዳለባቸው መልዕክቱን ያስተላልፋል።

# ስማዕድን ዘርፉ የተሰጠውን ትኩረት ታሳቢ ያደረገው ረቂቅ የማሻሻያ አዋጅ

ስምስም መንግሥቱ

ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ለ13 አመታት በሥራ ላይ የቆየውን የማዕድን ሀብት ልማት አዋጅ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ረቂቅ የማዕድን አዋጅ ተዘጋጅቷል፡፡ ረቂቅ የማሻሻያ አዋጁ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ምክር ቤቱም ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መርቶት ሲታይ ቆይቷል፤ ሰሞኑን ደግሞ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተመርቶ ውይይት ተደርጎበት የተለያዩ ሃሳቦችን መሰብሰብ ተችሏል፡፡

**የረቂቅ ማሻሻያ አዋጁ መነሻ**

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ሐብታሙ ተገኝ፤ አዋጁን ማሻሻል ያስፈለገበትን ምክንያት ሲገልጹ፤ አዋጁ ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ የነበረ ቢሆንም፤ የኃላፊነትና የባለሥልጣናት እንዲሁም የአስፈጻሚ ተቋማት መቀያየሮች በመኖሩ ምክንያት በተለያየ ጊዜ በተወሰኑ የአዋጁ አንቀጾች ላይ ከተደረጉ የማሻሻያ እርምጃዎች ባለፈ አዋጁ የተሟላ አልነበረም፡፡ የተወሰኑ ማሻሻያዎችን እያደረጉ ከመቀጠልና በተለያዩ ምክንያቶች እንዲሁም መንግሥት ለዘርፉ ከሰጠው ትኩረትና ከተሰጠው ኃላፊነት አኳያ እንዲሁም ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት የአዋጁ መሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፤ ዘርፉ ብዙ ጠቀሜታዎችን እንደሚያስገኝ እምነት ተጥሏል፡፡

‹‹የማዕድን ዘርፉ በሚፈለገው ልክ ሀገራዊ ጥቅም አላስገኘም፡፡ ለመጠቀም ስንፈልግ ደግሞ በፍትሐዊ መሆን ይኖርበታል›› ያሉት ሚኒስቴሩ፤ ይህ ሲባል የፌዴራል መንግስቱን፣ የክልሎችንና የማህበረሰቡን አጠቃላይ እንደ ሀገር ያለውን እኩል ተጠቃሚነት እያረጋገጡ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ማዕከል ያደረገ ወይንም የሚያስተካክል አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ ነው በሚል አዋጁን ማሻሻል አስፈልጓል፡፡ በማለት አስረድተዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በረቂቅ አዋጁ የልዩ ፈቃድ ማዕድን ልማትን ማስቀረት፣ የደለል ማዕድን ማምረት ፈቃድን ለውጭ ዜጋ መስጠትን ማስቀረት፣ የባህላዊ ማዕድን ማልማት የሥራ ፈቃድ ጊዜን ማሻሻል፣ የከፍተኛ ደረጃ ኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ለፌዴራል መንግስት እንዲሰጥ ማድረግ በረቂቅ ማሻሻያ አዋጁ ከተካተቱ መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

ለማዕድን ልማት ፈቃድ ሲሰጥ የፌዴራል መንግስቱና የክልሎች ድርሻ፣ ልማቱን ማስተዳደር፣ ከልማቱ ከሚገኘው ገቢ ክልሎች ተጠቃሚ ስለሚሆኑበት ሁኔታ፣ አካባቢን መልሶ ማልማትና የማህበረሰብ ተጠቃሚነት ከዚህ ቀደም በህጉ ውስጥ ያልነበሩ እንደሆኑ ሚኒስትሩ ጠቅሰው፣ አዋጁ ከሌሎች ህጎች ጋርም ተጣጥሞ መዘጋጀቱን አመልክተዋል። ከተጠቃሚነት አንጻርም ፌዴራል መንግስት በሚያስተዳድራቸው ፈቃዶች ክልሎች የሚያገኙት ሮያሊቲ እንዳልነበረ ጠቅሰው፣ በአሁኑ የተሻሻለው ረቂቅ አዋጅ ላይ መካተቱን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ቀደም አካባቢ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋርም ተያይዞ ክፍተቶችና የአፈጻጸም ችግሮች እንደነበሩ አመልክተዋል፡፡

አዋጅ ማውጣትና ማሻሻል ብቻውን በቂ እንዳልሆነና ወደ ተግባር መቀየር እንደሚያስፈልግ ያስገነዘቡት ሚኒስትሩ፤ ጥሩ ውጤት ለማግኘትም አፈጻጸሙ ላይ ጠንክሮ መሥራት ይገባል ብለዋል። ታች ላይ ያለው ተቋም ጠንካራ አለመሆን፣ የፀጥታ ችግር፣ በዘርፉ ላይ የአንዳንድ አካላት ጣልቃ ገብነት ችግሮችም ሌላው የዘርፉ ተግዳሮቶች እንደሆኑ በመጥቀስ፤ በህግና ፖሊሲ የሀገር ዜጋን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን የውጭ ባለሀብትንም ለመሳብ የአዋጁ መሻሻል ጠቃሚ እንደሆነ አስገንዝበዋል፡፡

በሰባት ክፍሎች የተደራጀውና 79 አንቀጾች ያለው ረቂቅ አዋጅ ከባህላዊ እስከ ከፍተኛ ማዕድን ማምረት የሚያካትት ወደ 51 አርቲክሎች (ገጾች) ሰፊውን ክፍል የያዘ ነው፡፡ ረቂቅ አዋጁ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግብዓቶችን በማከል እንዲያፀድቀው ያስተላለፈው ሲሆን ምክር ቤቱ ደግሞ በዝርዝር እንዲመለከተው ለኢንዱስትሪና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቶት፣ ለረቂቅ የተሻሻለው አዋጅ ማዳበሪያ የሚሆን ሀሳብ ከባለድርሻ አካላት ተሰብስቧል፡፡

> **የማዕድን ዘርፉ በሚፈለገው ልክ ሀገራዊ ጥቅም አላስገኘም። ለመጠቀም ስንፈልግ ደግሞ በፍትሐዊ መሆን ይኖርበታል። ይህ ሲባል የፌዴራል መንግስቱን፣ የክልሎችንና የማህበረሰቡን አጠቃላይ እንደ ሀገር ያለውን እኩል ተጠቃሚነት እያረጋገጡ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ማዕከል ያደረገ ወይንም የሚያስተካክል አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ ነው በሚል አዋጁን ማሻሻል አስፈልጓል**

ቋሚ ኮሚቴው ባደረገው ጥሪ መሠረትም ዘርፉን ከሚመሩ የክልልና የፌዴራል ተቋማት የተውጣጡ የሥራ ኃላፊዎች፣ አልሚዎችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ሀሳብ መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን፤ ከተሰጡት የግብአት ሀሳቦችም የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

**የክልል የዘርፉ መሪዎች ሀሳብ**

የኦሮሚያ ማዕድን ልማት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ዘውዱ ታደሰ፤ በአዋጁ በተወሰኑ የረቂቅ ድንጋጌዎች ከሕገ መንግሥቱና ሀገሪቱ ከምትከተለው የፌዴራሊዝም ሥርአት፣ ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው ከማስተዳደር፣ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 52(1) (መ) ላይ በሰፈረው መሠረት ማዕድንን ጨምሮ የተፈጥሮ ሀብትን ለማስተዳደር ከተሰጣቸው ሕገ መንግሥታዊ ስልጣን እንዲሁም ከክልሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች አንጻር ወደፊት አዋጁን ከመተግበር አኳያ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ማየታቸውን አንስተዋል፡፡

በማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚው የሥራ ዕድል መፍጠር በረቂቅ አዋጁ እንደ አንድ ዓላማ መያዙን በመጥቀስ፣ ነገር ግን የማዕድን ልማት በሚካሄድበት አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ቅድሚያ የሥራ እድል የሚያገኝበትና ከልማቱም ተጠቃሚ የሚሆንበት አግባብ በአዋጁ መስፈር እንዳለበትም አመልክተዋል፡፡

በረቂቅ አዋጁ ላይ የፌዴራል መንግሥት በማንኛውም ባለ ፈቃድ ከሚካሄድ የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ አምስት በመቶ ሥራው በሚካሄድበት ክልል ደግሞ ሁለት በመቶ ድርሻ ያለምንም ክፍያ ተብሎ የተቀመጠውንም አቶ ዘውዱ የፌዴራል ድርሻ ከፍ ማለቱ አሳማኝ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡ በልማቱ ለአካባቢ ተጽእኖ ተጋላጭ የሚሆነው የክልሉ መንግሥት እንደሆነ በመጥቀስ የበለጠ ድርሻ የክልሎች መሆን እንዳለበት አመልክተዋል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መሬት ለማዕድን ሥራዎች ክፍት ይሆናል ተብሎ በማሻሻያ ረቂቁ የተጠቀሰውንም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታቸውን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የማዕድን ሥራን እንደመርህ ማስቀመጡን ጠቅሰው፣ እንደገና መታየት እንዳለበትም ጠቁመዋል፡፡

ማዕድን ሚኒስቴር ለሀገር ጥቅም አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት ማናቸውንም መሬት የማዕድን ሥራ የሚካሄድበት ነው ብሎ መከልከል ይችላል ተብሎ በረቂቁ የተቀመጠውም የመሬት አስተዳደር ጉዳይ እንደሆነና ይህም መሬቱን ለማስተዳደር በሕገ መንግሥቱ ስልጣን ለተሰጠው አካል መተው ያለበት እንጂ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የሚወሰን እንዳልሆነም አመልከተዋል፡፡

የአማራ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሌ አበበ በበኩላቸው፤ በረቂቅ አዋጁ ላይ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በስፋትና በጥልቀት እንዲወያዩበት ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል ሲሉ ገልጸው፣ የሚሻሻለውን ረቂቅ አዋጅ ከማዘጋጀት በፊት 678/2002 የነበረው አዋጅ ጠንካራና ደካማ ጎን ላይ የዳሰሳ ጥናት መሥራት ያስፈልግ እንደነበርም ነው ያመለከቱት፡፡ በቀጣይም በረቂቅ የማሻሻያ አዋጁ ላይ ሰፊ ውይይት ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ የማሻሻያ ረቂቅ አዋጁ መንፈስ ክልሎች ያላቸውን ስልጣን ወደ ፌዴራል መንግስቱ መውሰድ እንደሆነ የገለጹት አቶ ኃይሌ፤ ከገቢ ጋር በተያያዘ በረቂቁ ላይ የተገለጸውን በተመለከተም ክልሎች ከሮያሊቲም ሆነ ከገቢ ግብር ከሚያገኙት የበለጠ በቀነሰ ሁኔታ በረቂቁ ላይ መስፈሩን ነው ያመለከቱት፡፡

የማሻሻያ ረቂቅ አዋጁ በሰባት ክፍሎች ተከፍሎ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቅሰው፣ ትኩረቱ የሚያጠነጥነው በሶስተኛው ክፍል ላይ ወይንም በአንድ ሀሳብ ላይ መሆኑን ነው የተናገሩት፡፡ ስለፈቃድ አይነቶች አሰጣጥ በሚያመለክተው ክፍል ሶስት ላይ ያተኮረ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ስለ ሥነ ምድር፣ ማዕድን ግመታ አይነት ሕገ ወጥ ቁጥጥርና ክትትል፣ የተጠቀሰ ነገር እንደሌለና ትንታኔ እንደሚጎለው አስረድተዋል፡፡

ከሀገራዊ ለውጥ በኋላ መንግሥት ትኩረት ከሰጣቸው መካከል አንዱ ማዕድን እንደሆነና ይህንን ተከትሎም ክልሎች የየራሳቸውን መዋቅራዊ አደረጃጀት በመሥራት መንቀሳቀሳቸውን አቶ ኃይሌ ተናግረዋል፡፡ ልማቱ ከለውጥ በፊትና ከለውጥ በኋላ የተገመገመበት ሁኔታ አንድ እንዳልሆነም በማውሳት፣ የተሻሻለው ረቂቅ አዋጅ የክልሎችን መልካም እንቅስቃሴ ታሳቢ ያደረገ ነው የሚል እምነት እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡ የማዕድን ሥራ በሕግ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ መስተጋብርም እንዳለው ጠቅሰው፣ በተለይም የማህበረሰብ ስምምነት አስፈላጊነት ግንዛቤ ሊያዝ እንደሚገባና መታየትም እንዳለበት ጠቁመዋል። በአጠቃላይ ረቂቅ አዋጁ ጥርጣሬን የሚያሳድር የግልጽነት ችግር እንዳዩበት ከነመፍትሄ ሀሳብ በዝርዝር በጽሁፍ ለቋሚ ኮሚቴው ማቅረባቸውንም ጠቁመዋል፡፡

የደቡብ ክልል ማዕድንና ኤጀንሲ ቢሮ የማዕድን ዘርፍ ኃላፊ አቶ እያሱ ማሞ፤ በከፊል የከበሩ ማዕድናት በአነስተኛ ደረጃ ለሚገኙት ፈቃድ የሚሰጠው በፌዴራል እንደሆነ በማስታወስ፣ በዚህ ደረጃ ፈቃድ ወስዶ በበቂ ሁኔታ የተንቀሳቀሰ ኩባንያ በየትኛውም ክልል አለመኖሩን እርግጠኛ መሆን የሚቻልበት ምክንያት መኖሩን ነው የገለጹት፡፡ በከፊል የከበሩ ማዕድናት በባህሪያቸው የሰው ጉልበት ካልታከለባቸው የሚከናወኑ እንዳልሆኑም ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ፍቃድ የመስጠቱ ኃላፊነት የክልል ሆኖ ሥራው ቢሰራ ውጤት ያመጣል የሚል እምነት ነው እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡

የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራም እንዲሁ በባህሪው ብዙ ሰዎች ጉልበታቸውን አቀናጅተው የሚያከናውኑት እንደሆነ በመጥቀስ፣ ካለው ነባራዊ ሁኔታ በክልሉ ሥራው ለማህበራት ብቻ እንዲሰጥ መደረጉን ገልጸዋል፡፡ ወርቅን የሚያህል ሀብት በግለሰብ ደረጃ እንዲለማ ፍቃድ መስጠት ተገቢነት እንደሌለውም አመልክተዋል፡፡ በአጠቃላይ ሊተገበር የማይችል ነገርን በአዋጁ ላይ ማስፈር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል በማለት ሃሳባቸውን አቅርበዋል፡፡

አቶ እያሱ ከካሳ ክፍያ ጋር በተያያዘም አርሶ አደሩ በሚኖርበት ስፍራ የሚገኝ ማዕድንን ጥቅም ላይ ለማዋል የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት በማይነካ መልኩ እንዴት መተግበር እንደሚቻል እንዲሁም የካሳ ክፍያው አፈጻጸምም ምን አይነት የማዕድን አይነት እንደሆነ በአዋጁ በዝርዝር መታየት አለበት የሚል እምነት አላቸው፡፡ ለእዚህም በድንጋይ ከሰል ማዕድን ላይ ያጋጠማቸውን ችግር ለአብነት ጠቅሰዋል፡፡

ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ኢንጂነር ፍቅሬ ኃይሌ፤ ክልሎች ያላቸው አዋጅና ደንብ መፈተሽ እንደነበረበት በመጥቀስ፤ በክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ ግልጽ የሆነ አዋጅ ባለመኖሩ ከድንጋይ ከሰል ማዕድን ጋር በተያያዘ ችግር ገጥሟቸው እንደነበር አንስተዋል። በፌዴራልና በክልል የሚሰሩ ሥራዎች ተለይተው በግልጽ መቀመጥ እንዳለባቸው እንዲሁም በግለሰብ ይዞታ ላይ የሚገኝ የማዕድን ሀብትን እንዴት መጠቀም ይቻላል የሚለውም ምላሽ ሊያገኝ እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡

ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ማስገባት የሚለው ግዴታ ለባህላዊ አምራቾች ብቻ ሳይሆን ኩባንያዎችንም ማካተት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡ የልዩ አነስተኛ ማዕድን ልማት ፈቃድን ማስቀረት በሚለው ላይ የአሰራር ሥርዓት ማበጀት እንጂ ማስቀረት በሚለው እንደማይስማሙም ነው የተናገሩት፡፡ በማዕድኑ ላይ የሚስተዋለውን ሕገ ወጥነት ለማስቀረት በገንዘብ ማበረታቻ ማህበረሰቡ ተባባሪ ሆኖ ሕገወጡን የሚያስይዝበት አሰራር የሚዘረጋበት ምቹ ሁኔታ በአዋጁ እንዲካተትም ጠይቀዋል፡፡

**የአልሚዎች ሀሳብ**

ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ ፕሮጀክታቸው የሚገኘው የኩርሙክ ወርቅ ማዕድን ኩባንያው አቶ መርዕድ አማረ ያነሱት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስን የተመለከተ ነው፡፡ በማዕድን ዘርፉ የተሰማሩ ኩባንያዎች በሌሎች ዘርፎች እንደተሰማሩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ሁሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማዕድን ሚኒስቴርና ገንዘብ ሚኒስቴር የተናበበ ሥራ እንዲሰሩ በማሻሻያ ረቂቅ አዋጁ በዝርዝር መታየት እንዳለበት አንስተዋል።

በሲሚንቶ ምርት ላይ የተሰማራውን ኢስት አፍሪካ ሆልዲንግ ኩባንያ ወክለው ሀሳብ የሰጡት አቶ ገዛኸኝ፤ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ለልማቱ ኃላፊነትን ወደ ላይ መውሰድ ሳይሆን፣ ወደ ማህበረሰብ እንዲወርድ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል። ሮያሊቲ ላይ ጭማሪ ሲደረግ ተጠቃሚው ላይ ሊያስከትል የሚችለው ጫናና ተያያዥ ጉዳይ የታየ ነው ብለው እንደማያምኑና ትንታኔ እንደሚያስፈልገው ተናግረዋል፡፡ ሮያሊቲ በማምረቻ ዋጋ ወይንም በመሸጫ ዋጋ ስለመሆኑም በግልጽ በድንጋጌው ላይ እንዳልተቀመጠም አመልክተዋል፡፡

ከሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ አቶ ቶላ መኮንን፤ ማዕድን በባህሪው ከፍተኛ ኢንቨስትመንትና ሰፋ ያለ ጊዜ እንደሚፈለግ ጠቀሜታውም ሰፊ እንደሆነ አንስተው፤ ከዚህ አኳያ በዘርፍ ውስጥ አብዛኛው ኢንቨስተር እንዴት ገብቶ ሊሰራ ይችላል፣ ለኢንቨስትመንቱ አሳሪ የሆኑ ነገሮችን ለይቶ ምቹ ነገሮችን በመፍጠር ሊከናወኑ ስለሚገባቸው ነገሮች ከሚሻሻለው አዋጅ ይጠብቁ እንደነበር ተናግረዋል። ከተረፈ ምርት በተሻለ ቴክኖሎጂ ማምረት እንደሚቻልና የወርቅ ተረፈ ምርት የማይደፋበት ማዕቀፍ ቢዘጋጅ የሚል ሀሳብ ሰጥተዋል።

**ማጠቃለያ**

የልዩ አነስተኛ ፈቃድን በተመለከተ ከጋዜጠኞች ለቀረቡ ጥያቄዎች የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ሐብታሙ ተገኝ፤ በሰጡት ምላሽ፤ በልዩ አነስተኛ ፈቃድ አወጣጥ የሚሉ አካላት ያልተፈቀደላቸው የውጭ ሀገር ዜጎች ጭምር በመሳተፍ የአካባቢውን ማህበረሰብንም ሆነ ሀገርን በሚጎዳ ሕገወጥ ድርጊት ላይ ተሰማርተው መገኘታቸውን አስታውቀዋል፡፡ የሀገር ሀብት በዚህ መንገድ ሲዘረፍ ማየት ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሰው፣ ይህንንም ሕግ በማስከበር መከላከል እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ሕገወጦቹ ገንዘብ በመስጠት ወርቁን ሌላ ቦታ እንደሚወስዱት ሚኒስትሩ ተናግረው፣ ማዕድን የማውጣቱ ስራ አካባቢው ላይ ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት ሳይታይ ማሽኖች ጥቅም ላይ እየዋሉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ባህላዊ አምራቾችን ማሳደግ ተገቢ ቢሆንም በዚህ መንገድ መሆን የለበትም ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ የማዕድን ሀገር ሆና ነገር ግን በሀብቷ ተጠቃሚ አይደለችም። ለአብነት ደቡብ አፍሪካ በአመት እስከ 123 ቶን ወርቅ ታመርታለች፤ ጋናም እንዲሁ እስከ ከ100ቶን በላይ ታመርታለች፡፡ በኢትዮጵያ 10 ቶን ወርቅ የተመረተው በጥቂት ወቅቶች ነው፡፡ አዋጁ ይህን ሁሉ ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ አዋጁ ከፀደቀ በኋላ የማስፈጸሚያ ደንብና መመሪያ አብሮ ይዘጋጃል በማለት ሕጎች የሚወጡት እየታዩ ካሉ ችግሮች መነሻ እንደሆነ ግንዛቤ ሊያዝ እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

የኢንዱስትሪና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶክተር አማረች በካሎ እና ምክትል ሰብሳቢው ዶክተር ፍቃዱ መንግሥቱ በየበኩላቸው በሰጡት ሀሳብ፤ ከቤቱ የተነሱት ሀሳቦች ግብዓት እንደሚሆኑና ቋሚ ኮሚቴውም በጥልቀት የሚያየው ጉዳይ እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡ አዋጁ በተቻለ መጠን የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ሀሳብ ያካተተ እንዲሆን በማድረግ ግልጽነት ያለው አዋጅ ጸድቆ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል ብለዋል፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ግጥምጥሞሽ

**በትረ ሙሴ (መልከ ሊትዮጵ)**

እንባቆም እባላለሁ፤ በህይወት ያለሁ ታሪካዊ ሰው ነኝ፡፡ በእርግጥ አባቴ የብዙ አጋጣሚዎች ባለቤት እንደሆነ ነግሮኛል፡፡ እናቴን እንኳን የተዋወቃት ሰርግ ቤት ወጥ ጨላፊ ሆና ስታሳልፍ እንደነበር አጫውቶኛል። ታላቅ ወንድሜ ሳይቀር ከሚስቱ ጋር ለቁም ነገር የበቃው በተሳሳተ ስልክ እንደሆነ አውቃለው፡፡ አንዳንዴ ከአባቴ የወረስኩት ይሆን እንዴ እላለው፡፡ ግን አይመስለኝም፤ እየሱስ እንዲህ ጽፎኝ ነው፡፡ እየሱስ ባይጽፈኝ እንኳን እሱ በተወው ባዶ ገጽ ላይ ራሴን አበላሽቼ ጽፌው ይመስለኛል፡፡

ከመጀመሪያ ፍቅረኛዬ ከትርሲት ጋር የተዋወቅነው በካርታ ጨዋታ ነበር፡፡ ካርታ ውሃ አጣጭ ሲሰጥ አስባችሁታል?

ወደ ህይወቴ የመጣችው ሁለተኛዋ ሴት ማክዳ ትባላለች፡፡ ዛሬ ላይ እንዴት ተዋውቀን እንዴት እንደተለያየን ሳስበው ይገርመኛል፡፡ የተዋወቅነው ሊፍት ውስጥ ነው፡፡ ለአባቴ የተላከ ዶክመንት ላደርስ ስድስተኛ ፎቅ ወደሚገኘው ቢሮው እየሄድኩ፡፡ ለምን እንደሆነ አላውቅም ሴት ስቀርብ ቀድሞ አፌ ላይ የሚመጣው ውሸት ነው፡፡ በእውነት መንገድ ተጉዤ የራሴ ያደረኳት ሴት የለችም፡፡ ማክዳንም ዋሸኋት፡፡ በካኪ ፖስታ የተሸፈነውን የአባቴን ዶክመንት እያሳየኋት ሲቪ ነው አልኳት፡፡ ስራ ልወዳደር እየሄድኩ እንደሆነ ዋሸኋት፡፡

በአዛኝ አይን አየችኝ፡፡ ይቅናህ የሚል በጎነት ከእሷ ወደእኔ ተላለፈ፡፡ አሁን ላይ ሳስበው እነዛ አይኖች ሊባርኩኝ ወደህይወቴ የመጡ መለኮታዊ አይኖች ነበሩ እላለሁ፡፡

ሊፍት ውስጥ እያለን ‹አንድ ነገር ብጠይቅሽ እሺ ትይኛለሽ› አልኳት፡፡

‹ምንድነው› አለችኝ በጠይም አይኖቿ ጠይም አይኔን እየቃኘች፡፡

‹እሺ የምትይኝ ከሆነ በአንቺ እሺታ ውስጥ የዛሬው ቅጥር ይሳካልኛል፡፡ እንቢ የምትይኝ ከሆነ ደግሞ ከዚህ በኋላ ምንም ነገር ተመኝቼ የሚሳካልኝ አይመስለኝም› አልኳት፡፡ ወደ አባቴ ቢሮ እየሄድኩ እኮ ነው፡፡ ድርጅቱ የአባቴ እኮ ነው፡፡

‹እኮ ምንድነው ልወቀው› በቅድሙ ትህትና ደግማ ጠየቀችኝ፡፡

‹እሺ ስትይኝ ነው የምነግርሽ› አልኳት

‹እሺ› ምንድነው፡፡

ልነግራት አፌን ስከፍት ሊፍቱ ስድስተኛ ፎቅ ደርሶ ውረዱ ሲል ተከፈተ፡፡ እኔ ስወርድ እሷ ቀረች፡፡ አባቴ ቢሮ ደርሼ ዳግም ልገናኛት ብዙ ጠበኳት፡፡ ግን አላገኘኋትም፡፡ በግምት ከስድስት ወር በኋላ ይመስለኛል አንድ ካፌ ቁጭ ብዬ ማኪያቶ ስጠጣ ከርቀት አየኋት፡፡ ደስ እያለኝ ነበር ሄጄ ያናገርኳት፡፡

‹አስታወሽኝ? አልኳት፡፡

እርግጠኝነት በጎደለው አካኋን ‹ሊፍት ውስጥ? አለችኝ፡፡ የማስታወስ ብቃቷን እያደነኩ ራሴን በአዎንታ ነቀነኩላት፡፡

‹ያን ቀን ግን ምን ልትነግረኝ ነበር እንደዛ ልቤን የሰቀልከው?

‹በነገርሽ ላይ ሁሉም ነገር አሪፍ ሆኗል፡፡ ያን ቀን አንቺ እሺ ባትይኝ ኖሮ አይሳካልኝም ነበር› ስል የውሸት ዘላበድኩ፡፡ ቀጥዬም ‹በድጋሚ የተገናኘነው በምክንያት ነው፡፡ ያን ቀን ቀንቶኝ ስራ ከጀመርኩ በመጀመሪያ ደሞዜ ራት የምጋብዛት የመጀመሪያዋ ሴት እንድትሆኚ ፍቃድ እየጠየኩሽ ነበር› ስላት በደንብ ሳቀች፡፡

በሚቀጥለው ቀን አሪፍ ራት ጋበዝኳት፡፡ ለስድስት ወር አብረን በፍቅር ቆየን፡፡ እንዴት እንደተለያየን ሳስበው ዛሬም ድረስ ያመኛል፡፡

ማክዳ የህይወት ዘመኔ ምርጥ ታሪኬ ናት፡፡ ነፍሷ በነፍሴ ውስጥ ዛሬም ድረስ አለች፡፡ ከህይወቴ ተሚጦ ያልወጣ እስትንፋሷን የምተነፍስ ይመስለኛል፡፡ በህይወቴ መጥተው ካለፉ ትናንትናዎች ውስጥ ዳግም እንድኖረው እድል ቢሰጠኝ እሷ ያለችበትን ትናንት እደግመው ነበር፡፡ ስንለያይ ለመጨረሻ ጊዜ ያልኳት አይረሳኝም፡፡ እንዲህ ነበር ያልኳት ‹አንቺ የታላቅ ነገር መጀመሪያ ነሽ፡፡ አንቺ የሌለሽበት ታላቅ ፍጻሜ የለም፡፡ አንቺ የደጋግ ነፍሶች ህልም፣ የመልካም ልቦች ራዕይ ነሽ። ከዚህ እስከዛ ጥግ የሌለሽ እግዚአብሄራዊ ሀቅ፡፡ ትንሹን ሰው ትልቅ አድርገሽዋል፡፡ ከፊትሽ ሳልሸሽ እንኳን ይቅርታ እንዳደረግሽልኝ አውቃለሁ፡፡ ከእንግዲህ ግን እንባቆም እንዳትይኝ የማረባ ነኝና ስምኦን ብለሽ ጥሪኝ፡፡ እንዴት ተለያያችሁ አትሉኝም? ከእለታት በአንዱ ቀን አራት ኪሎ ከሚገኝ ካፌ ውስጥ ቁጭ ብያለሁ፡፡ አባቴን በሞት ካጣሁ ወዲህ የመኖር ትርጉሙ ጠፍቶኝ ግራ የተጋባሁበት ሰሞን ነበር፡፡ በልጅነቴ ውስጥ በወጣትነቴም ውስጥ ሳይሞት ስለሚኖረው አባቴ እያሰብኩ ትካዜ ላይ ነበርኩ፡፡ ከፊት ለፊቴ ጠረጴዛው ላይ ሞባይሌ፣ የመኪና ቁልፌና ግማሽ ያደረኩት ማኪያቶ ይታየኛል፡፡ እና ደግሞ ማንም ያልተቀመጠበት ባዶ ወንበር፡፡ መኪናዬ መንገድ ዘግታ ኖሮ ፓርኪንግ የሚሰራ አንድ ወጣት መኪናዬን ከመንገድ ላይ ዘወር እንዳደርግለት ነግሮኝ ከሀሳቤ እስከመለሰኝ ጊዜ ድረስ ሁሉ ነገሬ ስለሆነው አባቴ እያሰብኩ ነበር፡፡ መንገድ የዘጋች መኪናዬን አንቀሳቅሼ ስመለስ ከፊት ለፊቴ ከነበረው ባዶ ወንበር ላይ የሴት ቦርሳ ተቀምጦ አየሁ፡፡

ቦታዬ ጋ እንደደረስኩ ማክዳ ደወለችልኝ፡፡ ስልኬ ሳይለንት ስለነበር ሲበራ ነው ያየሁት፡፡ ጥሩ ስሜት ላይ ስላልነበርኩ አላነሳሁትም፡፡ ጠዋት ከቤት ስወጣ ከክፍለ ሀገር የምትመጣ ጓደኛ አለችኝ አስተዋውቅሀለው እንዳለችኝ ትዝ አለኝ፡፡ ወዲያው ስልኬ በርቶ ሲጠፋ አየሁት፡፡ ‹የት ነክ? ሩቅ ካልሆንክ የሆነ ቦታ እንድታደርሰኝ ነበር› የሚል የማክዳን መልዕክት አየሁት፡፡ ሩቅ ቦታ ነኝ ብዬ ስላሰብኩ ሳልመልስላት ወደ ትካዜዬ ተመለስኩ፡፡ አፍታ ቆይቼ ቀና ስል ከፊት ለፊቴ ባዶው ወንበር ላይ መላዕክ ትሁን ሰው የማትለይ አሳሳች ሴት ተቀምጣ አስተዋልኩ፡፡ ትካዜዬ ድራሽ አባቱ ጠፋ። ከቁጥጥሬ ውጪ የሆነ ‹ዋው! የሚል የአድናቆት ድምጽ ከአንደበቴ ሲወጣ ትዝ ይለኛል፡፡ ቀይ ናት። ወደቢጫነት የሚያደላ፣ ታጥቦ የተሸለተ የሚመስል አንጸባራቂ ጸዐዳ ቆዳ አላት፡፡ እንደ ሰባት ሰዐት ጀምበር አትዩኝ የሚል ውበት፡፡

አይን የሚፈሩ የሚመስሉ አይኖች አሏት፡፡ ደም የመሰለ፣ በንጋትና በመምሸት መካከል ያለ ከንፈር። የተለያዩ ቀለማት ያወዙት ርጥብ ከንፈር ከሰልካካ አፍንጫዋ ግርጌ ይታየኛል፡፡ እና የሸሚዟን አዝራር ጥሰው ያጮለቁ ጡቶች፡፡ ያ ቀን ማክዳን ካየሁበት ቀጥሎ ባልመሸ ያልኩት ሌላኛው ቀን ሆነ፡፡ ሴት ስቀርብ መጀመሪያ የሚመጣልኝ ውሸት ነው ብያችሁ የለ፡፡ ለዚች ሴት የሚሆን ሁነኛ ውሸት ሳስብ የሆነ ነገር ትውስ አለኝ፡፡ ወንበሬን ይዤ ወደተቀመጠችበት ሄድኩ፡፡ ስታየኝ በትንሹ ደንገጥ ብላ ተረጋጋች፡፡

‹ጠባቂዎችሽ የሉም? አልኩ ዙሪያዬን እየቃኘሁ።

‹የምን ጠባቂ? ስትል ግራ ለመጋባት ሞከረች፡፡

‹መቼም ይሄ ውበት ያለጠባቂ ነው የሚንቀሳቀሰው ትይኝና አመት እንዳልስቅ› አልኳት፡፡

ሳቀች...የትም ያልተሰማ ውብታም ሳቅ፡፡

በሳቋ መግባት እንዳለብኝ አሰብኩ፡፡ ዘፍጥረት ታወሰኝ በሄዋን ሳቅ ሞት እንደመጣ፡፡ ጊዜ አላጠፋሁም ‹ከዛሬ ጀምሮ ያለምንም ክፍያ ለውበትሽ ዘብ ልቆም ራሴን አዘጋጃለሁ› አልኳት፡፡

‹ደስ ይለኛል› አለችኝ፡፡

እሺታዋን ተንተርሼ ‹አንድ ነገር ብጠይቅሽ እሺ ትይኛለሽ? ስል ጠየኳት፡፡

‹ምንድነው? አለችኝ ምንም ቢሆን እንቢ አልልህም በሚመስል አኳኋን፡፡

‹እሺ የምትይኝ ከሆነ በአንቺ እሺታ ውስጥ የሚከናወኑልኝ ብዙ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ እንቢ የምትይኝ ከሆነ ደግሞ ከዚህ በኋላ ምንም ነገር ብመኝ አይሳካልኝም›፡፡

‹እኮ ምንድነው ንገረኝ?

‹እሺ የምትይኝ ከሆነ ነው የምነግርሽ›

‹እሺ ምንድነው?

ልነግራት አፌን ስከፍት ስልኳ ጮኸ፡፡ በምልክት ይቅርታ ብላኝ ስልኩን አነሳችው፡፡ ከሆነች ሴት ጋር ስታወራ ሰማሁ፡፡ የቱጋ ነሽ? ያለቻት ይመስለኛል፡፡ ያለንበትን ካፌ ስም ስትነግራት ሰማሁ፡፡

ስልኩን ዘግታ ‹እሺ ምን ነበር ንገረኝ› አለችኝ፡፡

‹ዛሬ በህይወቴ የምፈልገውን ስራ የጀመርኩበት ቀን ነው፡፡ በመጀመሪያ ደሞዜ የምጋብዛት የመጀመሪያዋ ሴት እንድትሆኚ እፈልጋለው› አልኳት፡፡

መስማማቷን በሳቋ ገለጸችልኝ፡፡ ስልክ እንቀያየር እደውልልሻለሁ› ከማለቴ ጓደኛዋ መጣች መሰለኝ እጇን አንስታ ስትጠራት አየሁ፡፡ ሁሉም ነገር እዚያ ጋር ተበላሸ፡፡ ለካ የማክዳ ጓደኛ ነበረች፡፡ ለካ ማክዳን እየጠበቀች ነበር፡፡ ለካ ጠዋት ከቤት ስወጣ ከክፍለ ሀገር የምትመጣ ጓደኛ አለችኝ አስተዋውቅሀለሁ ያለችኝ እሷን ነበር፡፡ ለካ ቅድም ስትደውልልኝ የነበረው እሷ ጋ እንዳደርሳት ነበር፡፡ ከማክዳ ጋር እንዲህ ባለው አጋጣሚ ተለያየን፡፡

# ዓለም አቀፍ

## በወረርሽኙ 370 ሚሊዮን ገደማ ተማሪዎች ከምገባ መርሃ ግብር ውጭ ሆነዋል ተባለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት በ150 ሀገራት የሚገኙ 370 ሚሊዬን ገደማ ተማሪዎች ከምገባ መርሃ ግብር ውጭ ሆነዋል ተባለ፡፡

በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርት ቤቶች መዘጋታቸውን ተከትሎ በመላው ዓለም በመቶ ሚሊዬን የሚቆጠሩ ተማሪዎች ከምገባ መርሃ ግብሮች ውጭ መሆናቸው ተነገረ፡፡ በመርሃ ግብሩ በታቀፉ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ይቀርብ የነበረ 39 ቢሊዬን ምግብ ሳይቀርብ መቅረቱንም የዓለም የምግብ እና የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅቶች አስታውቀዋል፡፡

መርሃ ግብሩ ተማሪዎች ጤናቸው ተጠብቆ ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉ የሚያስችል ነበረ፡፡ ሆኖም በወረርሽኙ ምክንያት በመቶ ሚሊዬኖች የሚቆጠሩ ተማሪዎች ከመርሃ ግብሩ ውጭ ሆነዋል፡፡

ዩኔስኮ የትምህርት ቤቶቹ መዘጋት በ199 ሀገራት በሚገኙ 1 ነጥብ 6 ቢሊዬን ተማሪዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ገምቶ ነበረ፡፡ በ150 ሀገራት የሚገኙ 370 ሚሊዬን ገደማ ህጻናት ከምገባ መርሃ ግብሩ ሊርቁ ይችላሉም ብሏል፡፡

በተጠናቀቀው የፈረንጆቹ ዓመትም የተስተዋለው ይኼው ነው፡፡ በትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ይቀርቡ የነበሩ 39 ቢሊዬን ምግቦች ሳይቀርቡ ቀርተዋል። ህጻናቱ በትምህርት ቤቶቻቸው በመደበኛነት ሲያገኟቸው ከነበሩ 10 ምግቦች 4ቱን ወይም 40 በመቶ ያህሉን ሳያጡ እንዳልቀረም ተገምቷል፡፡

ይህ ሁኔታ በአንዳንድ ሀገራት ከፋ ያለ ነው። በመደበኛነት ሲያገኟቸው ከነበሩ 10 ምግቦች ዘጠኙን የሚያጡም አሉ ከዓለም የምግብ ፕሮግራም እንደተገኘው መረጃ፡፡ የተማሪዎች ምገባ መርሃ ግብርን ተግባራዊ ያደረጉ በርካታ ሀገራት አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ህንድ፣ ብራዚል፣ ቻይና፣ ደቡብ አፍሪካ እና ናይጄሪያ ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚሰለፉ ናቸው፡፡

የምገባ መርሃ ግብሩ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ በሚገኝ ቤተሰብ ውስጥ የሚያድጉ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት ያመጣል ለትምህርት ያበረታታልም። ሆኖም ወረርሽኙ 24 ሚሊዬን ገደማ ህጻናትን ከትምህርት ውጭ እንዳያደርግ ዩኒሴፍ እና የዓለም የምግብ ፕሮግራም ሰግተዋል፡፡

ኢትዮጵያም በተለያዩ ጊዜያት መርሃ ግብሩን ለመተግበር ሞክራለች፡፡ ከ3 መቶ ሺ የሚልቁ ተማሪዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ በማሰብ ባለፈው ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተጀመረው መርሃ ግብር በወረርሽኙ ቢፈተንም አሁንም ተጠናክሮ ስለመቀጠሉ ከአስተዳደሩ የተገኙ መረጃዎች አመልክተዋል ሲል አል አይን ኒውስ ዘግቧል፡፡

## በናይጄሪያ ጀልባ ላይ በተከሰተ አደጋ 100 ሰዎች ሲሞቱ በርካቶች የደረሱበት አልታወቀም

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ባለፈው ሰኞ በደቡብ ምዕራባዊ ናይጄሪያ ሰዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ የነበረ ጀልባ ሰጥሞ ከ100 በላይ ሰዎች ሲሞቱ በርካቶች የገቡበት አለመታወቁን ባለሥልጣናት ተናግረዋል።

ጀልባው በአንድ ሰርግ ላይ የታደሙ ወደ 300 የሚጠጉ መንገደኞችን ካዋራ ከተባለችው የናይጄሪያ ግዛት ወደ ሌላኛው ኒጀር ግዛት በማጓጓዝ ላይ ሳለ ነበር የሰጠመው። ሰዎችን የማፈላለጉና ነፍስ የማድን ተግባሩም ቀጥሏል።

ጀልባው ባጋጠመው ችግር ምክንያት በውሃ የተጥለቀለቀ ሲሆን ላጋጠመው ችግር መነሻው ያ እንደሆነ ፖሊስ ገልጿል። የሟቾችን ቁጥር በተመለከተ የተለያዩ ቁጥሮች እየወጡ ይገኛሉ።

የካዋራ ግዛት ፖሊስ 106 ሰዎች እንደሞቱና 144 ሰዎችን ደግሞ መታደግ እንደተቻለ ገልጿል። ጨምሮም ከሟቾች ውስጥ ግማሽ የሚሆኑት ኢቡ ከተባለ መንደር እንደመጡና ሌሎች 38 ሟቾች ደግሞ መነሻቸው በአቅራቢያው ካለ ደዝካን ከተባለ መንደር ነው ብሏል።



ቀደም ብሎ አደጋው ያጋጠመት አካባቢ ባህላዊ መሪ ኡመር ቦሎጊ ከ150 በላይ ሰዎች ሞተዋል ተብሎ እንደተሰጋ ተናግሯል። በርካታ ሴቶች ከአደጋው ልጆቻቸውን ለማትረፍ ሲሞክሩ መሞታቸውን ከአደጋው ከዳኑት መካከል አንዱ ሞሃመድ አልሃሰን ለቢቢሲ ገልጿል።

የሞሃመድ እህት ከአደጋው ብትተርፍም የ7 ዓመት ልጇን ግን በአደጋው አጥታለች። ሌላኛዋ ከአደጋው የተረፈችው አይሻ ሞሃመድ በቅርቡ ሊሞሽሩ የነበሩ ሦስት ልጆቿን በጀልባው አደጋ እንዳጣች ተናግራለች።

በአደጋው የቅርብ ዘመዱን ያጣው ሞሃመድ ሳሊሁ "ክስተቱ እጅግ አሳዛኝና ማኅበረሰቡን እጅግ ያስደነገጠ ነው" ሲል ለኤኤፍፒ የዜና ወኪል ገልጿል። የአደጋው መነሻ አሁንም እየተጣራ ይገኛል።


የአካባቢው ፖሊስ የጀልባው ክፍል ጉዳት በመድረሱ ጎርፍ በመፍጠር ጀልባው እንዲጥለቀለቅና እንዲገለበጥ ምክንያት ሆኗል ብሏል። ሆኖም የአካባቢው ባህላዊ መሪ ማዕበል ጀልባውን መትቶ ወንዝ ውስጥ ከወደቀ ዛፍ ጋር እንዲጋጭ ምክንያት በመሆኑ ጀልባዋ ተገልብጣለች ብለዋል።

የካዋራ ግዛት አስተዳዳሪ የተሰማቸውን ሀዘን ለተጎጂ ቤተሰቦች ገልጸው የጠፉትን ሰዎች የማፈላለጉ ስራ ይቀጥላል ብለዋል። አስተዳዳሪው ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች ትላንት ረቡዕ የጎበኙ ሲሆን 100 ሺህ የመንሳፈፊያ ሰደሪያ እንደሚሰጡና የአደጋ ጊዜ ትምህርት እንደሚጀመር ቃል ገብተዋል።

የናይጄሪያው ፕሬዝዳንት ቦላ አህመድ "በካዋራ የዜጎቻችንን ሕይወት በቀጠፈው በዚህ እጅግ አሳዛኝ ክስተት በጥልቅ አዝኛለሁ" ብለዋል። "ተጎጂዎቹ የሰርግ እድምተኞች ሆነው እንዳለመታደል ይህ አይነት አደጋ ላይ መውደቃቸው ክስተቱን እጅግ አዛሳኝ ያደርገዋል" ሲሉም አክለዋል።

በናይጄሪያ ወንዞች ላይ ጀልባ አደጋ ሲያጋጥማቸው መስማት የተለመደ ነው።

# ስፖርት



## ኢትዮጵያ ስኬታማ የጎልፍ ቻምፒዮና አስተናገደች

ዓለማየሁ ግዛው

በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት ከግንቦት 29 እስከ ሰኔ 4 2015 ዓ.ም በመከላከያ ፋውንዴሽን አዲስ አበባ ጎልፍ ክለብ ሲካሄድ የቆየው የአፍሪካ ቀጣና አራት (ሪጅን4) የጎልፍ ስፖርት ቻምፒዮና በስኬት ተጠናቋል፡፡ የኢትዮጵያ ጎልፍ አሶሴሽን ከዝግጅቱና ውድድሩ በርካታ ልምዶች መውሰዱንም ገልጿል፡፡

ቻምፒዮናው በኢትዮጵያ ጎልፍ ስፖርት አሶሴሽን፣ በመከላከያ ፋውንዴሽን እንዲሁም በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አዘጋጅነት የተካሄደ ሲሆን፤ ኢትዮጵያን ወክሎ በውድድሩ የተሳተፈው ቡድንም ጥሩ እንቅስቃሴ በማድረግ ተፎካካሪ እንደነበረ ታውቋል። ይህም ቻምፒዮናውን ከማዘጋጀት ከተገኘው ተሞክሮ በተጨማሪ ለኢትዮጵያ ጎልፍ ስፖርት ተወዳዳሪዎች ዓለም አቀፍ ልምድ እንዲኖራቸው ማስቻሉ ተጠቁሟል፡፡

ከዚህ ቀደም እንዲዚህ ዓይነት ትልቅ ውድድር አዘጋጅቶ እንደማያውቅ ያስታወሰው አሶሴሽኑ፤ በቀጣናው ከተዘጋጁ ውድድሮች የኢትዮጵያ ከፍተኛ እንደሆነም ገልጿል፡፡ ይህም በትልቅነቱ በቀጣና ደረጃ ከተዘጋጁ ቻምፒዮናዎች ክብረወሰን በመያዝ ኢትዮጵያ የተሻለ አዘጋጅ ሀገር ሆና እንድትመረጥ ማድረጉ ተጠቁሟል፡፡ የአፍሪካ ጎልፍ ኮንፌዴሬሽን ለኢትዮጵያ የተሳካ የውድድር ዝግጅት አድናቆቱንና ምስጋናውን መግለፁም ታውቋል፡፡ ኢትዮጵያ ለውድድሩ ከተቀመጠው ደረጃ በላይ ተዘጋጅታ ማስተናገዷ ቻምፒዮናው የተዋጣለት እንዲሆን ማድረጉን አሶሴሽኑ ገልጿል፡፡

"ጎልፍ በኢትዮጵያ ይስፋፋል፤ ኢኮኖሚያችንንም ይደግፋል" በሚል መሪ ሃሳብ የተካሄደው ይህ ቻምፒዮና ዋና ዓላማው ታዋቂ የጎልፍ ተጫዋቾችን በቀጣናው አገራት ማፍራት ነው። የጎልፍ ስፖርትን በመላው ሀገሪቱ በማስፋፋት ለኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ስፖርተኞችን ለማፍራት የሚያበረክተው አስተዋጽኦም ከፍተኛ ነው፡፡



የአፍሪካ ዞን 4 የጎልፍ ቻምፒዮናን ኬንያ በበላይነት አጠናቃለች፤

በዘንድሮው ቻምፒዮና በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና አራት ስር የሚገኙ ዘጠኝ አገራት ለተሳትፎ ቢጠበቁም 5 ሀገራት ብቻ ውድድሩ ላይ ተገኝተዋል፡፡ እነዚህም አገራት ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ርዋንዳ፣ ታንዛኒያና ዩጋንዳ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ እራሷ ደጋሽ በሆነችበት ውድድር ስኬታማ ዝግጅት ብታደርግም በውድድር ተሳትፎ ግን ተወዳዳሪዎች ውጤት ሊቀናቸው አልቻለም። ያም ሆኖ የተገኘው አራ ተኛ ደረጃ አበረታች ነበር። ኢትዮጵያውያን ጎልፍ ተጫዋቾች በዓለም አቀፍ ደረጃ የመወዳደር ልምድ ባይኖራቸውም በችሎታቸው እና ለማሸነፍ ያደረጉት ፉክክር ሁሉንም ተሳታፊዎች አስገርመዋል።

የቻምፒዮናው አሸናፊ ኬንያ ስትሆን፤ ሁለተኛ ዩጋንዳ፣ ሶስተኛ ርዋንዳና አዘጋጇ ሀገር ኢትዮጵያ በአራተኛነት መፈጸም ችላለች። ከዚህም አሶሴሽኑ ብሔራዊ ቡድኑን ለማብቃት ሰፊ ስራ መስራት እንዳለበት ልምድ መወሰዱን ጠቁሟል። ጥሩና ልምድ ያለው ብሔራዊ ቡድን ለመገንባት ብዙ ውድድሮች ላይ ተሳትፎ ማድረግ እንደሚኖርበትም አስቀምጧል፡፡

የአዲስ አበባ ጎልፍ ክለብ አሰልጣኝና ተጫዋች አክሊሉ ኃይሌ፣ ብሄራዊ ቡድኑ ብዙ ችግሮች ቢኖሩበትም ጥሩ ዝግጅቶችን ማድረጉን ያስረዳል። ብሔራዊ ቡድንን በመወከል በምስራቅ አፍሪካ መጫወት ከጀመረ አስር አመት እንዳስቆጠረ ገልጾም፤ በዚህም ብዙ ልምድ ማካበት እንደቻለ ተናግሯል፡፡ ብሔራዊ ቡድኑ ከተወዳዳሪዎቹ ጋር ለመፎካከር ቢሞክርም በልምድ ማጣት ብልጫ እንደተወሰደበት የሚናገረው አክሊሉ ፤ ለዚህም እንደ ምክንያት ሊወሰድ የሚችለው በቂና ደረጃውን የጠበቀ የጎልፍ ሜዳ አለመኖር መሆኑን ጠቁሟል። ኢትዮጵያ ውስጥ የጎልፍ ሜዳ እጥረት በመኖሩ ብሔራዊ ቡድኑ ውድድር ጠንካራ ተፎካካሪ እንዳይሆን ምክንያት ሊሆን ችሏል ሲልም አክሏል።ከሌሎች ሀገራት ጋር ተፎካካሪ ለመሆን ብዙ ስራዎች መሰራት ይኖርባቸዋል ባይ ነው፡፡ ስፖርቱ እንዲስፋፋ ትኩረት ተሰጥቶ የግንዛቤ መፍጠር ስራዎች መሰራትና ተተኪዎችን በስፋት ማፍራት ላይ መስራት ያስፈልጋል ሲልም አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡

የኢትዮጵያ ጎልፍ አሶሴሽን ፕሬዚዳንት አቶ ተሾመ ሞሲሳ ዝግጅቱን አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ፣ ‹‹የአፍሪካ ቀጣና አራት የጎልፍ ተጫዋቾች ስብስብ ለኢትዮጵያ ጎልፍ እድገትና ለምናፈራቸው ታዳጊ ጎልፍ ተጫዋቾች የቃልኪዳን ማህተም ነው›› ሲሉ ተናግረዋል። ኢትዮጵያ ቻምፒናውን ማዘጋጀቷ ለጎልፍ ስፖርት ታላቅ የምስራችና መሰረት እንደሆነም ጠቁመዋል። የውድድሩ ዝግጅት ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የጎልፍ ፍኖተ ካርታ ውስጥ የመካተቷ ማስረጃ እንደሚሆንም ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በራሱ ሜዳ እንደመጫወቱ ትልቅ እድል የነበረው ቢሆንም፤ የዓለም አቀፍ ውድድር ልምድ ማጣቱ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ ሌሎች ሀገራት በርካታ ውድድሮችን የሚወዳደሩ በመሆናቸው ጥሩ ልምድና የአሸናፊነት ስነልቦና የበላይነት ሊወስዱ ችለዋል። ለዚህም ኢትዮጵያ ብዙ የጎልፍ ተጫዋቾችን ለማፍራት ብዙ ሜዳዎችን ለመገንባት ትኩረት መስጠት እንዳለባት የአፍሪካ ጎልፍ ኮንፌዴሬሽን አስተያየት መስጠቱንም ፕሬዚዳንቱ ገልፀዋል፡፡


### ማስታወቂያ

ቀደም ሲል መዳን በክርስቶስ ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን (MEDAN BEKRISTOS ALEM AKEF BETEKRISTIAN) ተብሎ ይጠራ የነበረው ኪንግደም ሲያንትስ አለም አቀፍ ቤተክርስቲያን (KINGDOM SAINTS ALEMAKEF BETECHRSTIAN) ተብሎ የተቀየረ ስለሆነ በዚህ ስያሜ እና ዓርማ ተቃውሞ ያለው አካል ካለ በ10 ቀን ወደ የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል እንዲቀርብ፡፡

**የኢትዮጵያ ወንጌል**
**አማኞች አብያተ**
**ክርስቲያናት ካውንስል**

### የጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ

ድርጅታችን ፍቅርተ ማርያም አጠቃላይ ንግድ ሥራ/ኃ/የተ/የግ/ማህበር የስብሰባ ጥሪ ለማድረግ ይፈልጋል ::

**የጠቅላላ የጉባኤው አጀንዳዎች**

1. የማህበሩን የሒሳብ ሪፖርት ማቅረብና በጀት ማጽደቅ
2. የአክሲዮን መዋጮ ጉዳይ በተመለከተ
3. የማህበሩን ቋሚ ንብረቶች ስለማሳወቅ

የስብሰባው ቀን ፡- 18/10/2015 ዓ.ም
ቦታ፡- በማህበሩ ጽ/ቤት
ሰዓት፡- ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት

**ፍቅርተ ማርያም አጠቃላይ ንግድ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር**

### ማስታወቂያ

**ማረፊያ አረጋውያን እንክብካቤ ድጋፍ ሰጪ ድርጅት** የተባለ አገር በቀል ድርጅት ከዚህ በፊት ይጠቀሙበት የነበረው ሎጎ ቀይሮ ከዚህ በታች በተቀመጠው አርማ የሚጠቀም መሆኑን እያሳወቀን

ማረፊያ MAREFIA
የአረጋውያን እንክብካቤ እና ድጋፍ

ተቃዋሚ ካለ እስከ ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ሕብረት ኢንሹራንስ ሕንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 406 ድረስ ከጠዋቱ 2፡30 ጀምሮ ማቅረብ የሚችል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**

### ማስታወቂያ

ትሮፒክስ ኮንሰልቲንግ ኢንጂነርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር በአሁን ሰዓት በባለሀብቶቹ ፍላጎት እና በኢትዮጵያ የንግድ ህግ መሰረት እንዲፈርስ ስለተወሰነ በድርጅቱ ላይ ማንኛውም የእዳ ጥያቄ ያለው መንግስታዊ መ/ቤት ድርጅት ወይም ግለሰብ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 /ሰላሳ/ ቀናት ውስጥ ቀርባችሁ ያላችሁን ጥያቄ በበቂ ማስረጃ አስደግፋችሁ ማመልከት የምትችሉ መሆኑን አስታውቃለሁ፡

**አድራሻ፡-** አ.አ ጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 08 ሸገር ግራንድ ሞል የቢሮ ቁጥር DS–158
**ስልክ ቁጥር፡-** 09-04-03-26-30

**ትሮፒክስ ኮንሰልቲንግ ኢንጂነርስ ኃ/የተ/የግል ማህበር**

### የሒሳብ ምርመራ አገልግሎት የጨረታ ማስታወቂያ

የኮንታ ልማት ማሕበር በደቡብ ም/ኢ/ሕ/ክ/መንግሥት በኮንታ ዞን የሚገኝና በኢትየጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ የተመዘገበ ሀገር በቀል ተራድኦ ድርጅት ነው:: በመሆኑም ማኅበሩ የሒሳብ እንቅስቃሴዎችን ሕጋዊ ፈቃድና እውቅና ባላቸው ኦዲተሮች ማስመርመርና ኦዲት ማስደረግ ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም እ.አ.አ ከጥር 1/2022 እስከ ታኅሣሥ 31/2022 ያለውን የአንድ ዓመት የሒሳብ እንቅስቃሴ ማስመርመር ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች የተመለከተውን መስፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ቀናት በደቡብ ም/ኢ/ሕ/ክልላዊ መንግሥት ኮንታ ዞን አመያ ከተማ ኮንታ ባሕል አዳራሽ ሕንፃ ውስጥ በሚገኘው ቢሮ ቁጥር 1 ቀርቦ ለዚሁ ጨረታ የተዘጋጀውን ሰነድ በመግዛት መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እያሳወቅን አመልካቾች ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው፤ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፤ የፋይናንስ እና የኦዲት ሙያ ምስክር ወረቀት ያላቸው እና ተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ መሆኑን ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው::

ስልክ ቁጥር፡-09 17-83-6103

**የኮንታ ልማት ማሕበር**

### የሙያ ምዝገባና ፈቃድ ሰርተፊኬት መጥፋት ማስታወቂያ

ፈይሳ ለማ ግዛው የሙያ ደረጃ በጁኒየር ነርስ ፕሮፌሽናል በምዝገባ ቁጥር BEFO/AHITQFFWO/1-9/896 በ10/02/2010 በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጤና ጥበቃ ቢሮ የተመዘገበ የሙያ ፈቃድ ሰርተፊኬት ጠፋብኝ ብለው በ05/10/2015 ዓ.ም ከፖሊስ በተጻፈ ማስረጃ አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም የተጠቀሰውን የሙያ ፈቃድ ሰርተፊኬት ወድቆ ያገኘ ወይንም በእዳ ይዤዋለሁ የሚል በአንድ ወር ጊዜ ካላመለከተ ተለዋጭ የሙያ ፈቃድ ሰርተፊኬት የሚሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን**

### ማስታወቂያ

"**ሶሻል ዲውቲ አልያንስ**" የተባለ አገር በቀል ድርጅት ቦርድ መር ሆኖ ለመመዝገብ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን የምዝገባ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ተቃዋሚ ካለ እስከ ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ህብረት ኢንሹራንስ ሕንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 406 ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ይቅረብ፡፡

**የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**